የካም መታሰቢያ

የኢትዮጵያ ፊደል መሠረትነት መታወቂያ

በ፷ወ፰ ዓመተ መንግሥቱ ለቀዳማዊ
ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ከአስረስ የኔሰው ዘብሔረ ጐጃም
ተጻፈ ።

በ፲ወ፱፻፯ወ፩ ዓመት እምልደተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

ቁጥር ...

አሥመራ በኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ታተመ ።

መ ግ ቢ ያ ።

ይህችን መጽሐፍ የምታነቡ ኢትዮጵያውያን አስጠነቅቃችኋለሁ ማለት ፡ ስለ ግዕዝ መሠረት ከፈረንጆች ጽሑፍ ላይ እየተቀበሉ የከምን መታሰቢያ ግዕዝን መሠረቱ በሌሎች ዓለማት ክፍል የማይገኘውን ከማያውቁት ቋንቋ ከጥንታዊው ግዕዝ ውሥጥ እየገቡ ተረጉመን እያሉ በፍጹም ሐሰት ጥንታዊውን የግዕዝ ፊደል መልክ ከቀኝ ወደ ግራ እያደረጉ ጽፈውት ይገኛል ። ከቀኝ ወደ ግራ መጻፋቸው ግዕዝ ከደቡብ ዓረብ የመጣ ነው ብለው ለፈጠሩት ፖለቲክ ድጋፍ እንዲሆናቸው ነው እንጂ ፡ እርግጠኛ አለመሆኑን እንድታውቁና እንድትጠነቀቁ አሳስባችኋለሁ ። በጠርነት የማይጋለቡ ቢሆን በስብከት ገብተው የኢትዮጵያን ታሪክ ሲደመስሱ ሲያፋልሱ ይገኛሉ ፡ እውቀታቸው እርግጥ ከሆነ ከብሉይ ኪዳን ውሥጥ የገደለውን ስለምን አልተረዱት ? ፡ ሳይረዱት ከኖረውም ከምሉ በክፍሉ ከ፱፬ኛው ክፍል ገሥግሬ እስከ ፳፯ኛ ክፍል መፀሐረሻ የጻፍኩትን በጥንቃቄ መመልከት ነው ።

የደቡብ ዓረብ የኢትዮጵያ ግዛት በመሆኑ በጥንታዊ ግዕዝ ፊደል የተጻፈውን የኢትዮጵያ ነገሥታት ለመታሰቢያ አቁመውት የነበረውን ሐውልት ጽሑፍ እያዩ ይህን ምክንያት በማድረግ የከምን ፊደል ለሴም ልጆች እየሰጡ መጻፍ ጀመሩ ፡ ለጽሑፋቸውም ተቀባይ እስከ ማግኘት ቻሉ ። የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ ፡ የግዕዝ ጥንታዊ የሳባ ፊደል የሚሉት ስም የወጣው በሐሰት ነው እንጅ እውነት አይደለም ፡ የዮቅጣን ልጆች የሀንድን ንጉሥ ብራህማ የተባለውን ገድለው ኢትዮጵያን ነፃ አወጡ የሚለውን ጽሑፍ ከማመን የውቅያኖስን ባሕር በሬ ጠምጂ አርሼ እህል ዘርቼ አርሚ አጭጂ ወቅቼ እህሉን በመሬት ላሉት ሸምቼ ብዙ ብር አገኘሁ ብሎ ቢጽፍ እንደ ማመን ያለ ነው ። ቋንቋ መልክ ነው ፡ መልክም ቋንቋ ነው ፡ ፊደል ሐውልት ነው ፡ ሐውልትም ፊደል ነው ፡ ፊደል መልክ ነው ፡ መልክም ፊደል ነው ፡ ፊደል አባት ነው ፡ አባትም ፊደል ነው ፡ ፊደል ልጅ ነው ፡ ልጅም ፊደል ነው ፡ ፊደል ወሰን ነው ፡ ወሰንም ፊደል ነው ፡ ፊደል ዓላማ ነው ፡ ዓላማም ፊደል ነው ፡ ዓላማ የሁራት ምልክት ነው ፡ ሁራትም ነፃነት ነው ፡ ነፃነት መንግሥት ነው ፡ መንግሥትም ኃይል ነው ፡ የኃይል መቆምያ ንጉሥ ነው ፡ የሕዝብ ክብሩ ንጉሥ ነው ፡ የንጉሥ ክብሩ የሕዝብ ብዛት ነው ፡ የሕዝብ ብዛት የንጉሦች ንጉሥ (ንጉሠ ነገሥት) መባልን ያመጣል ፡ የማነኛውም ነገር መጠቅለያ ፊደል ነው ። መንግሥት ከለው ፊደል አለው ፡ ፊደል ከለው መንግሥት አለው ፡ መንግሥት ሲጠፋ ፊደልም አብሮ ይጠፋል ፡ ይህንም የማያውቅ የለም ።

እስከ ዛሬ በካም ቤት ከወረደው መንግሥትና ፊደል የንጉሠ ነገሥትነቱ ስምና ግዕዝ ሳይደመሰሱ በመቄየታቸው የማይቀና የለም ፡ ይህም ንጉሠ ነገሥትነት ከምሥርና ከሊቢያ የተረፈውን የአፍሪቃ መሬት አልፎ ከሴም አገር የዓረብን አገሮች ሁሉ እስከ ፮፻ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በአክሱም ከተማ ግብራቸውን ሲያቀርቡ እንደኖሩ ታሪክ ይነግረናል ። ስለዚህ ይህ ዛሬ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚጠሩበት «ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» የሚለው ስም በግዕዝ የተጻፈ ከካም ገሥግሮ እስከ

ዛሬ ፬ሺ ፰፱ ዘመን የቆየ ለመሆኑ ምስክሩ ግዕዝ ነው ፡ የግዕዙም ምስክር ንጉሥ ነገሥት የሚለው ስም ነው ። የፖሊቲክ ሰዎች ሲለፉ ሲደክሙ የሚታዩ ይህን የማዕርግ ስም የዘመን እርዝማኔ ለማሳጠር ነውና የኢትዮጵያ ልጆች ተጠንቀቁ ፡ የግዕዝን መጻሕፍት አትናቁ በግዕዝ መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጥቅም ለማግኘት ትችላላችሁ ፡ የጥንታዊ ማዕድንን በታዎችንና የሀገራችሁን የክብር መገገብ ለማግኘት ትችላላችሁ ፡ የውጭ አገር ሰዎች ጥንታውያኑን መጻሕፍት በውድ ዋጋ ሲገዙ ለምን ፈለጉት ይመስላችኋል ? የውጭ አገር ሰዎች ለፖለቲክ የጻፉትን ለመቀበል ያደረሰ የውጭ አገር ሰዎች የግዕዝን መጻሕፍት በሰፊ ካለመመርመር የተነሣ ነው ። የውጭ አገር ሰዎች የግዕዝን መጻፍሕት ምሥጢሩን እናውቃለን ይላሉ ። ቢሆንም ለኢትዮጵያ ልጆች ተርጉሞና ጽፎ መስጠት ከድፍረት የሚቈጠር ነው ፡ እርግጠኛ ችሎታ የሌላቸው መሆናቸውን የሚያስረዳው ከ፬፱ኙ መጻሕፍተ ብሉያት ውሥጥ የተዝረከረከውን መርምረው አለ መረዳታቸው ነው ። ስለዚህ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ በድንገት ጠቅሰዉት ከሚገኝ በተቀር በሙሉ የኢትዮጵያን ታሪክ ጻፍን የሚሉት ፖለቲካ መሆኑን እንድታውቁ አሳስባችኋለሁ ፡ ስለ ማነኛውም " ትቤ አክሡም ,, በተባለው መጽሐፌ ተመልከቱ ።

አስረስ የኔ ሰው ፤

የ ካ ም መ ታ ሰ ቢ ያ

መ ቅ ድ ም ።

እኔ ይህችን የካም መታሰቢያ የምትባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ ያሰብኩበት ምክንያት ፡ የኢትዮጵያን ውበትና ሀብት በጥብቅ የሚመለከቱ ሰዎች ሁሉ ባፍ ወዳጅ እየመሰሉና ውሥጥ ውሥጡን የኢትዮጵያን ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት አድክመው ፡ እነሱ የኢትዮጵያን ታሪክ ለመደምሰስና ክብሯን ለመውሰድ ስለሆነ ፡ አስቀድመው ለሥራ ረዳት የሚሆናቸውን ሲያክወናውኑ በየጊዜው ይታያሉ ። ኢትዮጵያን አዲስ ቅኝ አገር ለማድረግ አሳባቸው ስለሆነ የኢትዮጵያን ክብር በመቀነስ ታሪኳን በማኳሰስ እየጻፉ ለዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ስላአስጠኑ ያነን ረቂቅ ፖለቲካ እርግጠኛ እየመሰላቸው ከዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ላይ እየተቀበሉ የኢትዮጵያ ልጆችም ጽፈው ለወጣቶቹ ሲያስጠኑ በማየቴ በተቻለኝ ለሀገሬ የረዳሁ መስሎኝ የኢትዮጵያን የታሪክ ክብር ቅድምናን ለወጣቶች ለማስጨበጥ እርግጠኛውን መረጃ ለመፈለግ በየገዳማቱ እየዞርኩ የተቻለኝን ያህል ስመረምር ድካሜን በየገዳማቱ የሚገኙት ያውቁታል ፡ እንደዚህም ደክሜ ያደራጀሁትን ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ መሠረት መሆኑን ከመረዳታቸው በፊት ፡ የጽሑፋችን መቃወሚያ አመጣጣን እያሉ ብዙዎቹ ሲቃወሙኝ ስለሚገኙ ፡ የገዛ ሀገራቸውን ታሪክ ራሳቸው ሲቀንሱ በማየቴ የጠላት ስብከት የድምፁ ኃይል ራሴን አበላሽብኝና ከ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. ወዲህ የአንጎል በሽታ አደረብኝ ። ከዚያም ወዲህ ያነኑ የጀመርኩትን ዓላማ አንደበቴ እስቲዘጋ አልተውም በማለት ለወጣቶቹ ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋ ግዕዝ የተቻለኝን ያህል እጽፋለሁ ። በዛሬው ዓለም ላይ በሚታየው በሰይጣናት መሪነት ለሰው መግደያ የሚሆን ከመሥራት ወደ ኋላ ቀርታ ስለታየች ፡ አስቀድሞ ከካም ዘመነ መንግሥት ገሮምሮ እስከ ዛሬ ፲፰፻፷፱ ዓ.ም. ዘመን ድረስ የቆየውን ታሪክ ሁሉ ለመደምሰስ ታስቦ በኢትዮጵያ ፊደልን ያመጡ የደቡብ ዓረቦች ግዕዝን አመጡ ፡ ያነንም አባ ሰላማ ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያሉትን የፊደል ደረጃዎች አሰናዳ ፡ መጻሕፍተ ብሉያትም በአባ ሰላማ ከጽርዕ ወደ ግዕዝ ተገለበጡ ይላሉ ። መጻሕፍተ ብሉያት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን በጭራሽ የካዱና ይህንም ትምህርት ያጠኑ ሰዎች በርክተዋል ። አሁን ለወጣቶቹ ለማስታወስ የምደክመው ስለ ፊደል መሠረትና ስለ መጻሕፍተ ብሉያት አመጣጥ ስለሆነ ፡ ፊደሎችም በየጊዜው እየተሻሻሉ እንደመጡ ፡ መጻሕፍተ ብሉያትም እንደዚሁ ንግሥት ማክዳ በሳባ ላይ ነግሣ በነበረ ጊዜ ፡ ከሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ገሮምሮ ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ እየተገለበጡ የመጡት እስከ ዛሬ የጥንታዊነት ምስክርነታቸውን ይዘው ይገኛሉ ። ኢትዮጵያ "ሳባ" ተብላ የተጠራች ፡ ሳባ የምትባል ሴት በሴም ዘር በራግው ዘመን ነው ፡ ራግው የነበረበት ዘመን በ፲፯፻፸፰ ዓመተ ዓለም ነው ፡ ኢትዮጲስ ከዚያ አስቀድሞ ነው ። መሠረታዊው ታሪክ በሰፊው በኋላ ይጻፋል ። አሁን ለጊዜው ስለ ግዕዝ መሠረት የእግዚአብሔር ምሥጢር መነጋገ

ሪያ መሆኑን እንድትረዱት እየገለጽኩ እጽፍላችኋለሁና በጥንቃቄ እንድትመለከቱት አቅርቤላችኋለሁ ።

ክፍል ፩

ቀዳሚ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ።

፩ኛ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ወደ ሥር ገብቼ አጋዕዝት ዓለምን ሰፈጥሩ የሆነውን መልአኩ ለሙሴ እየነገረው እንደጻፈው ሰመረመር ፥ ፭ድ የነበረው ቋንቋ እስከ ባቢሎን ግምብ እስከ ፸፬፻፸፯ ዓ. ዓለም ነው ። በዚያን ጊዜ በሶ፱ቱ አለ ቆች ልክ ሶ፱ ቋንቋ ተለይቷል ፥ የኢትዮጵያን ፊደል እናስተካክላለን የሚሉ ከሶ፱ቱ ቋንቋ ዎች ገሥመረው እስካሁን ሳይለወጥ የቆየ ቋንቋ አምጡ ተብለው ቢጠየቁ በቂ መልስ የላ ቸውም ። ሙሴ የጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ በሚታየው በቀላል ግምት ከ፯፻ ቋንቋ በላይ ተጽፎ ይገኛል ። የዚህ ሁሉ ቋንቋ ቃሉ ብቻ የተለየ ሰሆን ፥ ያ፩ነትን ምስክርነት ይዘው የሚገኙ ምዕራፍና ቁጥር ናቸው ። ምዕራፍና ቁጥር ባይኖሩ ግን ማነኛውም በምን ይታ ወቅ ነበር ? ። እንደዚሁም የሰው መልክ ቢ፫ት ዓይነት ቀለም የተለየ ሲሆን ፥ በቁጥር ግን ፭ድ ሆኖ ይገኛል ፥ መጽሐፍ ቅዱስም በሚያስረዳን መሠረት ፥ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከአብራይስጥ ወደ ግዕዝ መልሰው ያመጥዋቸው መጻሕፍቶች ፥ ፩ኛ ሄኖክ የጻፈውን መጽሐፈ ሄኖክ ፥ ፪ኛ ሙሴ የጻፈውን ኩፋሌና ፮ቱን ብሔረ አሪት ናቸው ። ሌሎችንም በየጊዜው ከአብራይስጥ ወደ ግዕዝ እየመለሱ አምጥተዋቸው የሚገኙ መጻሕፍ ቶች እርግጠኛውን የቁጥር ትርጓሜ ይዘው ይገኛሉ ፥ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች የፊደ ልን ቁጥር የለም ለማለት ሲሞክሩ ለግብዞችም ሲጽፉና ሲያወሩ ይገኛሉ ። ጽሑፋቸ ውና ወሬአቸው ከንቱ ነው ፍሬ ያለው አይደለምና ፥ ለግብዞች የጊዜ መግፊያ አንዲሆን እንተወው እንጅ እግዚአብሔር የመሃንዲሶች አባት መሆኑ የማይክድ ሊሆን ፥ አጋዕዝት ዓለምን ሲፈጥሩ በቁጥር አይደለም ማለት ከእንስሳ የሚያስቈጥር ነው ፥ ቁጥር መኖሩ የታመነ ሲሆን ቁጥሩ በምን ፊደል እንደነበረ ለማወቅ መመርመርና መፈለግ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ አለ ። እንግዲህ የቁጥርን ነገር እንዳንዘነጋ ማስታ ወሻዎችን ከቅዱስ መጽሐፍ ውሥጥ እናምጣ ።

፩ኛ ሙሴ አሪቱን ሰ፪ምር "በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ,, ሲል በ ብሎ ስለምን ገሥመረ የሚል ቢኖር ፥ አሪ. ዘፍ. ፩ ፫ ፥ ወይቤ እግዚእ ፥ ፯ ፱ ፲፩ ፲፬ ፥ ፳ ፳፬ ፳፯ ፳፱ ፱ መሆናቸውን እናስተውል በ ፱ ቁጥር ነው ።

፪ኛ ፥ በ፩ኛ ም. በ፩ኛ ቁ. "በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ,, ሰማየ ሲል ሰ. ፥ ወምድረ ሲል መ. እነዚህ ፪ቱ ፊደሎች በግዕዝ ፊደል ቁጥር ሰ ሰበት ሰማ ዮች ፥ መ መሬት ፥ ማይ ፥ እሳት ፥ ነፋስ ፬ት ማለት ነው ። እነዚህ ቁጥሮች የተገባ የም ሥጢር ትርጓሜ ይዘው የሚገኙ በግዕዝ ፊደል ነው ከላይም በ ብሎ የገሥመረበ

ትን ምሥጢር ለመረዳት ከላይ ከ፫ት ፳፱ ወይሴ እግዚእ ከለው ከ፱ኛ በ ፱ኛ ቍጥር መሆኑን እናስተውል ።

፫ኛ ፡ ፩ ፭ "ወሰመዮ እግዚአብሔር ለብርሃን ዕለተ ወለጽልመት ሌሊተ,, ሌትም ሆነ ንጋትም ፩ኛ ቀንም ተባለ ፡ ፰ . . . ፱ኛ ቀንም ሆነ ፡ ፲፫ ፡ . . . ፫ኛ ቀንም ሆነ ፡ በነ ዚህ በ፫ቱ ዕለታት ጽልመትና ብርሃን ሲፈራረቁ ቆዩ እንጅ የጨለማውና የብርሃኑ መሥፈሪያ ገና ከአጋዕዝት ልቡና ተገልጸ ለመላእክትም አልታየም ነበር ፡ በ፬ኛው ቀን ግን ጨረቃ ዐሐይና ከዋክብት ተፈጥረዋል ፡ ማለት የሌሊቱም ቍጥር የመዓልቱም ቍጥር እንዲታወቅ የዛሬ መሃንዲሶች ሜትር እንደሚሠሩ የሌትና የቀን መለኪያዎች ዐሐይ ጨረቃና ከዋክብት ተፈጠሩ ። እንግዲህ ቍጥር ዓለም ሲፈጠር አልነበረም ለማ ለት የሚሞክሩ ሰዎች እዚህ ላይ ምን ይመልሳሉ? ፡ ቍ ፲፬ ፡ በሌትና በቀን መክኸል ፡ ለም ልክት በቀኖች በወሮች በመዶች ምልክት እንዲሆኑ ያለው እነዚህ ሁሉ ቍጥሮች አይደሉም ለማለት የሚቻል ይሆንን ።

፬ኛ ፡ ፪ ፪ . . . «ወአዕረፈ እግዚአብሔር በሳብዕት ዕለት» ይላል ፡ ሳብዕ ሲል የግዕዙ ፊደል ቍጥር ሰ ፯ ነው ።

፭ኛ ፡ ፪ ፯ "ወንብሮ እግዚአብሔር ለሰብዕ እምነ መሬት ምድር ወነፍሐ ውስተ ገጹ መንፈሰ ሕይወት,, ባለው መሠረት ሲተረጐም ፡ መሬት መ ፬ ወነፍሐ ካለው ፫ት ድምር ፯ት ፡ ሰብዕ ሲል ፯ት ነገሮች ያሉበት ማለት ነው ብሎ የሚተረጕም በግዕዝ ፊደል ነው ።

፮ኛ ፡ ፪ ፲፮ ወአዘዘ እግዚአብሔር ለአዳም ያለው ፡ አዳም ሲል በግዕዝ ፊደል አ ፵ ደ ፫ ፡ መ ፬ ፡ ድምር ፶፵፬ ይሆናል ፡ ይህም ፶፵፬ ቍጥር ጥልቅ ምሥጢር ያለው መሆኑን ለመረዳት ፡ ራዕየ ዮሐ ፲፬ ፩ እይ ። ፶፵፬ሺ የሚለው ፶፵፬ቱ የአዳምን የስሙን ቍጥር በሽ አብዝቶ መሆኑን መመልከት ነው ።

፯ኛ ፡ ሔዋን ሲል በግዕዝ ፯፩ ነው ፡ ፯፩ ቍጥር የዓመቱ ቀኖች ሩብ ነው ፡ ፯፩ን ለ፯ት ስትመድበው ፲፫ ሰንበት ታገኛለህ ፡ ፲፫ት ቍጥር ሰላም ነው ፡ የሰላም ቍጥር ፲፫ ነው ።

፰ኛ ፡ አሪ ዘፍ ፯ ፲፯ «ወከነ እይኅ ላዕለ ምድር» ይላል አይኅ በግዕዝ ፊደል አ ፵ ፡ የ ፯ ኅ ፰ ፡ ድምር ፶፱ ይሆናል ። ይህንም ለመረዳት ፰፬ ቍ "ወተለዓለ ማይ መልዕልተ ምድር ፻ወ፱ ዕለተ,, ያለውን እይ ፡ ወደላይ ከፍታውንም በቍ ፰ « ፲ ወ፭፻ ተለዓለ መልዕልቶመ ማይ» ፡ ከተራሮች በላይ ፻፱ ቀኖች ረግቶ የቆየው ውኃ ከፍታው ፭ሽ፭፻ እንደነበረና ፭ሽ፭፻ ያለው ፻፱ውን በ፻ አብዝቶ መሆኑን ከላይ በአዳም ስም እንደ ተገለጸው ማስ ተዋል ነው ። በቅዱሳት መጻሕፍት ውሥጥ በማብዛትና በመቀነስ የቍጥር ምሥጢር መኖሩን ማስተዋል ታላቅ ጥቅም ነው ።

፱ነኛ ፡ አ ዘፍ ፲፯ ፭ "ወኢይሰመይ እንከ ስምከ አብራም ኦላ ትሰመይ አብርሃም,, ብሎ ፭ኛ ፊደል ጨመረለት ፡ ይህም በግዕዝ ፊደል አብራም ሲል አ ፵ ፡ በ ፱ ፡ ረ ፪ ፡ መ ፬ ፡ ድምር ፶፱ ነበር ፡ ግን ፶፱ ቍጥር ለ ፺ ፭ የገደለው ስለ ሆነ ፡ በግዕዝ ፊደል ፭ኛ ቍ የሆነውን ሀን ጨመረለትና አብርሃም ሲል የስሙ ቍጥር ፺ ሆነ ፡ ፺ ቍ ዋና

መሠረት ስለ ሆነ ነው ፡ ጀን ለፅት ሲመድቡት ፲፪ ይሆናል ፡ ከጀ ቀጥር ፲፪ት ፅት እንደ ተገኘ ከአብርሃምም ፲፪ቱ ነገደ ፭ኤል እንዲወለዱለት ሲአመለክት ነው ።

፲ኛ ፲፫ «ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ሣራ ብእሲትከ ኢትሰመይ እንከ ሣራ አላ ይኩን ስማ ሳራ» አለው ፡ እንደዚህ ማለት የፊደል ስሚ በግዕዙ ፊደል ቁጥር ሣ ፭ ቁ. የነበረው ቀርዶ በግዕዙ ፊደል ሰ ፯ ቁ. የሆነውን ይሁን ሲል ነው ፡ ሳራ ሲል ሰ ፯ ፡ ረ ፮ ፡ ድምር ፲፫ ይሆናል ፡ ፲፫ ቁ. ከላይ እንደተጻፈው የሔዋንን ስም ፯፩ ከለው ለ፯ ሲመ ደብ ፲፫ ስለሚሆን ፲፫ ቁጥር ዋና መሠረት ስለሆነ መሆኑን መረዳት ነው ። ግን በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የፊደሉን ቁጥር ትርጓሜ ያልተረዱ ሰዎች አማርኛውን ሲተረጉሙ የሚስትህ ስም ሰራ አይባል እንግዲህ ስሚ ሳራ ይባል ብለው ጽፈውት ይገኛል ። ምክንያቱም የፊደል ቁጥር ትርጓሜ የሚያውቁ ሰዎች በልክ ስለሆኑ ነው ።

ክፍል ፪

፲፩ኛ ፡ አ ዘፍ. ፳፰ ፲፪ «ወሐለመ ወይሬኢ ሰዋስወ ውስተ ምድር» ፡ ይላል ሰዋስው ሲል በግዕዝ ፊደል ሰ ፯ ፡ ወ ፮ ፡ ሰ ፯ ፡ ወ ፮ ፡ ድምር ፸፬ ይሆናል ፡ ፸፬ቱን ለ፯ት ስትመድበው ፲፱ ይሆናል ፱ኙ ቁጥር የእመቤታችን ስም ፡ ፲ሩ የወልድ ማለት ነው ።

፲፪ኛ ፡ አ ዘፍ ፴፪ ፳፰ ፡ «ወይቤሎ ኢይኩን እንከ ስምከ ያዕቆብ ፡ ዳዕሙ ይኩን ስምከ እሥራኤል» ያለውን በግዕዝ ፊደል አ ፵ ፡ ሠ ፩ ፡ ረ ፯ ፡ ዐ ፸ ፡ ለ ፬ ፡ ድምር ፻፳፫ ይሆናል ከ፻፳ ውሥጥ ስንት ፳ ይገኛል ፯ ፡ ስንት ፲ ይገኛል ፲፬ ፡ ስንት ፩ ይገኛል ፳፬ ድምር ፵፬ ይሆናል፡ ማቴ. ፪ ፲፮ እይ ። ይህም ፵፬ት ቁጥር ከአብርሃም ገቦሮ እስከ ጌታችን ያለው ትውልድ ነው ፡ ፫ቱ ትርፎች ከአብርሃም እስከ ያዕቆብ ያለውን ትውልድ ፲፬ ፲፬ የሚለው ነው ፡ "እስመ ክህልከ ምስለ እግዚአብሔር ወምስለ እጓለ እመሕያው" ያለውን ቍ. ማቴ. ፩ ፪-፲፮ . ያለውን ተመልከት ።

፲፫ኛ አ. ዘፀ. ፯ ፫ «ዘአስተርአይኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ እስመ አም ላክመ· አነ ወስምየ እግዚአብሔር» ያለው በግዕዝ ፊደል አነ ሲል አ ፵ ፡ ነ ፶ ፡ ድምር ፺ ይሆናል ፡ ወስምየ እግዚእ ያለው አ ፵ ፡ ገ ፪ ፡ ዘ ፯ ፡ አ ፵ ድምር ፫፻፷ ይሆናል ይህም በጨረቃ ሲቆጠር ያመቱ ቀኖች ቁጥር ነው ።

፲፩ኛ ፡ ፲፪ ፴፯ «ወግዕዙ ደቂቀ እሥራኤል እምራምሴ ውስተ ሰከታ ፭፻፸ አጋር» ያለውን የኢትዮጵያ ሊቃውንት አሪቱን ከእብራያስጥ ወደ ግዕዝ ሲመልሱ የግዕዙን ፊደል ቍ. ፭፻ ነግነት መሆኑን ሲገልጹ እሥራኤል ከባርነት ወደ ዕረፍት ጉዞ ሲገሥምሩ "ግዕዙ" አሉ ። ይህም ያዕቆብ ወደ ግብጽ ሲወርድ ፸፭ ነፍስ ሆኖ ስለነበር ፡ ሲወጡ ግን ፸፭ቱ ፭፻ ፭፻ ቁ. ስለሆኑ ነው ፡ ወደ ግብጽ ወርዶው በባርነት ሥራ የቆዩትን ፸፭ቱን ቍጥርና የግዕዙን ቍ. ፊደል ከ፭ሽ፭ የወጣውን ፭፻ ቍጥር ፡ በ፸፭ቱ ስታበዛው ልክ በአሪቱ እንደተጻፈው ፭ ሽህ ታገኛለህ ፡ የኢትዮጵያ ፊደል የመሠረቱ ጥልቅነት እስከ ዚህ ነው ።

፲፭ኛ ፡ አ ዘፍ. ፲፫ ፬ "እስመ በዛቲ ዕለት ትወጽኡ አንትሙ በወርኃ ሃሌ ሉያ" ፡ ሲል

ሀ በግዕዝ ፊደል ፩ኛ ስለሆነ፡ እሥራኤልም የሚወጡ ዓለም በተፈጠረበት በሚያዝያ ፩ኛው ወር ነውና ፩ኛውን ወር በ፩ኛው ፊደል ስም ጠሩት ።

፲፯ኛ፡ አ ዘፍ ፳፬ ፳፫፡ «መሀሎ ሙሴ ቅድመ እግዚእ ፵ ዕለተ ወ፵ ሌሊተ፡ እክለ አ.በልዐ ወማየ አ.ሰትየ» ፡ ወጸሐፈ ውስተ ጽላት ዘንተ ፲ተ ቃለ ይላል ። ይህም በጽላቱ ላይ ፲ቱ ቃላትን ጻፈ ሲል ፲ተ ብሎ ፡ ደግሞ ቃለ ያለው በግዕዙ ፊደል ቀ ፫ ፡ ለ ፱ ድምር ፲ር ነው ።

፲፯ኛ ፡ አ. ዘዳ. ፱ ፲፩ ፡ በ፵ ዕለት ወበ፵ ሌሊት ወሀበኒ እግዚአብሔር ፪ተ ጽላተ ዘእ ብን ጽላተ ዘከ.ዳን ይላል ፡ ጽላተ እብን ሲል አ ፵ ፡ በ ፱ ፡ ነ ፴ ፡ ድምር ፸፱ ፡ ይህም ፵፱ኙ የአብ ፡ ፲ሩ የወልድ ፡ ፸ው የመንፈስ ቅዱስ ድምር ፸፱ ነው ። ዘከ.ዳን ያለውም ከ.ዳን ሲል በግዕዝ ፊደል ከ ፺ ፡ ዳ ፱ ፡ ነ ፶ ፡ ድምር ፪፻ ይሆናል ፡ ከ፪፻ ስንት ፸ ይገኛል ፱ ፡ ስንት ፲ ይገኛል ፲፮ ፡ ስንት ፭ ይገኛል ፴፭ ድምር ፷፫ ነው ፡ ይህን ለ፯ት ስትመድበው ፱ ይሆናል ፡ ፱ኙ ከ.ዳናት ማለት መሠረቱ ይህ ነው ፡ ከ.ዳንና መሐላ ትር ጓሜው ፩ድ መሆኑን ለማስረዳት መሐላ ሲል መ ፬ ፡ ሐ ፫ ፡ ለ ፪ ፡ ድምር ፱ ይሆናል ።

፲፮ኛ ፡ ኦሪ. ዘኢ.ያሱ ፡ ፯ ፮ ወበአ ኢ.ያሱ ጎበ ካህናት ወይቤሎሙ ንሥኡ ታቦተ ሕግ ወ፯ቱ ካህናት ይንሥኡ ፯ተ መጣቅዕተ ዘኢ.ዮቤል ያለው ፡ ኢ.ዮቤል» ሲል በግዕዝ ፊደል ቁጥር አ ፵ ፡ የ ፯ ፡ በ ፱ ፡ ለ ፪ ፡ ድምር ፻፵፩ ። በ፻፵ ውስጥ ስንት ፸ ይገኛል ፯ ፡ ስንት ፲ ይገኛ ል ፲፩ ፡ ስንት ፭ ይገኛል ፶፭ ፡ ድምር ፵፱ ይሆናል ። ከ፵፱ኙ ዓመቶች ፯ት ንኡሳን ሰንበቶች ይገኛሉ ።


የቀኖች ቁጥር ፫፻፶፩ ነው ፡ ደግሞ ፫፻፶፩ቱ ፡ ለሰባት ተመድበ ፶፪ ፶፪ት ይገኛል ፡ የ፯ን ፶፪ ልክ ፫፻፶፩ ዓመት ይሆናል ይህችም ዓመተ ኅድገት ፶ኛዋ ዓመት ናት ።

፲፱ነኛ ዜና መዋ. ራብዕ ፸፪ ፸ ... ወአንተ ኢ.ትሕንጽ ቤተ ለስምየ እስመ ብዙኃ ደመ ከዓውከ በዲበ ምድር ቅድሜየ» ይላል ቅዱስ ዳዊት ቤተ መቅደስን ልሥራ ብሎ ቢጸልይ አንተ የብዙ ሰው ደም በምድር ላይ በፊቴ ስታፈስ ነበርና የስሜን መኖርያ ቤት አንተ አትሠራም አለው ። «ወናሁ ወልድ ይትወለድ ለከ ወዝንቱ ይከውን ብእሴ ዕሩፈ ወአ፵ርፎ እምኵሉ ጸላእቱ እለ ዓውዱ ፡ ሰሎሞን ይሰመይ ስሙ ፡ ወሰላመ ብዙኃ ወጽማዌ እሁብ ላዕለ ፸ኤል በመዋዕሊሁ ይላል ፡ እንግዲህ የዚህ ምሥጢር ስንመረምረው ካን ተ የሚወለደው ሰው አራፊ ይሆናል ዕሩፍ ሲል ፊደሉን መመልከት ነው ፡ ፀ በእብ ራይስጥም በግዕዝም ፊደል ፈዓ ነው የዕረፍት ነገር የተገሠሠው ለሰንበት ስለሆነ ወአ ፵ርፎ ሲል ፊደሎችን መመልከት ነው ፡ ስሙንም ሰሎሞን ይባላል ያለውን ፡ ሰሎ ሞን ሲል ሰ በኢ.ትዮጲስ ፊደል ፯ ቁጥር ነው ። እንግዲህ የሰሎሞን ስም የምሥ ጢር ትርጓሜውን ይዘ የሚገኘው በክም ቤተ መንግሥት ሲያያዝ በወረደው ሆኖ ሲገ ኝ ይህን ተመልክተው የግዕዝን ምሥጢር በሰፊው በመከተል ፋንታ ልዩ ምክንያት የሚፈጥሩ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ዋጋ ያገኙ ይሆን ? ።

፸ኛ ፡ ነገሥት ፯ ፱ ወውእቱ ቤት ዘሐነጸ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ፫ በእመት ኑ ኁ ፡ ያለውን ስንመረምር ፫ ቁ. ከላይ እንደ ተመለከተው የአብርሃም ስም ቁጥር መሠ

ረቱ ጥልቅ ምሥጢሩ ረቂቅ ስለሆነ ፡ ፮ በእመት ኑኑ ያለው ፮ው ክንድ በጋት ፫፻፷ ነው ፡ ይህም ፩ዱ ክንድ ፮ት ጋት ስለሆነ ነው ፡ የ፮ት ቁጥር መሠረትነቱ ስለ ክንድ ለማነኛውም መስፈሪያ ክንድ ስለሆነ ፡ የመሥፈሪያን ነገር ጠንቅቆ ማወቅ አስፈላጊ ነው ፡ ክንድ ማለት በግዕዝ እመት ማለት ነው ፡ በግዕዙ ፊደል ቍጥር አ ፴ ፡ መ ፬ ፡ ተ ፲ ፡ ድምር ፶፬ ነው ፡ ይህን ለ፮ ስትመድበው ፶ ይሆናል ፡ ፶ ማለት በግዕዝ ፊደል ቍጥር በ ነው ። ስለዚህ ሙሴ አሪቱን በቀዳሚ ብሎ ገ፫መረው ፡ ፶ኝን ባ፲ ሲአበዙት ፭ ይሆ ናል ፡ ፭ናን ባ፬ት ሲአበዙት ፫፻፷ ይሆናል ፡ ይህም ፫፻፷ የእግዚአብሔር ስም መሆ ኑን ለመረዳት አ. ዘፀ. ፮ ፫ ፡ ዘአስተርአይኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ እስመ አምላኮሙ አነ ፡ ሲል ፡ አ ፴ ፡ ነ ፴ ፡ ድምር ፸ ፡ ወስምየ እግዚእ ሲል ፡ አ ፴ ፡ ገ ፬፻ ፡ ዘ ፹ ፡ አ ፴ ፡ ድምር ፫፻፷ መሆኑን መረዳት ነው ።

፭፩ኛ ፡ ፫ ነገሥ. ፲ ፲ ፡ ወወሀበቶ ለሰሎሞን ፯ወኧ መክሊተ ወርቅ» ይላል ፡ ፯ኧን ለ፮ት ስትመድበው ፭ ይሆናል ፡ ፭ው፦ ፩ድ እያልክ ፮ቱ ፯ኧ ነው ፡ የከሎው መሠረት ለመከንዳትም ቢሆን ፮ት ቍጥር ዋና ነው ፡ ይህም በግዕዙ ፊደል መክሊት ሲል ፡ መ ፬ ፡ ከ ፱ ፡ ለ ፪ ፡ ተ ፲ ፡ ድምር ፷፮ ይሆናል ፡ ከላይ ፩ዱ ክንድ ፮ት ጋት ነው ብየ አመልክ ፫ለሁ ፡ ደግሞ አ. ዘፀ. ፭፩ ፲ ፡ ወትገብር ታቦተ ዘመርሙል ዘዕፅ ዘኢይነቅዝ ዘከዕበ እመት ወመንፈቀ እመት ፡ ፡ ይላል ፡ ዘከዕበ እመት ሲል ፪ ክንድ ወመንፈቀ እመት ሲል ፫ት ጋት ፪ቱ ክንድ ፲፪ት ጋት ነው ፡ ከ፫ቱ ጋት ሲደመር ፶ ጋት ይሆናል ፡ ፭ቱ ክንድ ፴ ጋት ፡ ፲ሩ ክንድ ፷ ጋት ፡ ፭ው ክንድ ፯፭ ጋት ፡ ፵ው ክንድ ፪፯፵ ጋት ፡ ፭ው ክ ንድ ፫፻፷ ጋት ይሆናል ። ስለዚህ ፀሐይ ስትጓዝ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ለምሳሌ በክንድ ፯ ፡ በጋት ፫፻፷ ነው ፡ ይህም ሥራው ትእምርተ መስቀል ሆኖ ነው ፩ቱ ማዕ ዝን ፩ ጊዜ ፯ ፫፻፷ ይሆናል ።



፩ዱ ፫፻፷ በመከከሉ ያለው መሥፈሪያ ነው ፡ ፪ኛው ፫፻፷ በዙሪያው ያለው መለ ኪያ ነው ፡ ድምሩ ፯፻፲ ይሆናል ፡ ይህም የደ ብረ ዕዮን የዳዊት አምባ ምሳሌ ነው ፡ ዕዮን ሲል በግዕዝ ፊደል ቍጥር ፀ ፯፻ ፡ የ ፯ ፡ ነ ፴ ድምር ፯፻፲ ይሆናል ።

የትነሣንበት ስለ ፮ት ቀ. ስለሆነ ፡ ፫፻፷ን ለ፮ት ስትመድበው ፯ ይሆናል ፡ የጨረቃ ንም ሠርቅ ለማወቅ ፯ው፦ ላ፩ት ስትመድበው ፲፭ ይሆናል ፡ ይህም በቀን ፩ቱ ክንድ ፡ በጋት ፭፩ት ስለሆነ ፡ በቀን ፲፪ ሰዓተ መዓልት ፲፪ ሰዓተ ሌሊት ፡ በቀን በቀኑ ፭፩ ሰዓ ቶች አሉ የሚባለው የመገኛው መሠረት ይህ ነው ፡ የጨረቃን ብተት ከለማወቅ ብዙ ጉድለት እንዳለበት ለማወቅ የሚቻልበት በር ይህ ነው ።

፳፪ኛ ፡ ስለ ቅዱስ ዳዊት ትንቢት ፡ ፩ ፩ ፡ ፍክሬ ዘጻድቃን ወዘኃጥኣን ፡ መዝሙር ዘዳ ዊት ሃሌ ሉያ ፡ ይህም የዳዊት ዝማሬ ፩ኛ ሲል ሀሌ ሉያ ብሎ ገ፫መረው ፡ መዝሙ ርም ዘመረ ካለው የወጣ ስለሆነ ፡ ዘመረ ሲል በግዕዝ ፌ. ዘ ፡ መ ፡ ረ ፤ ድምር ፯፩ ነው ። ፯፩ ቍጥር ስለ ሰንበት ሱባዔ የሚቆጠርበት ያመቱ ሩብ ማለት መሆኑን ከላ ይ አመልክቻለሁ ። ፯፩ መሆኑን ለማረጋገጥ መዝሙር ፴፪ ፪ ፡ ወበመዝሙር ዘበሠርቱ አውታሪሁ ፡ አለ ፡ በሠርቱ ሲል በ ፫ ፡ ሠ ፭ ፡ ረ ፯ ፡ ተ ፲ ፡ ድምር ፯፩ ፡ ይህን መመል ከት ነው ። አውታሪሁ ሲልም ፡ አ ፴ ፡ ወ ፵ ፡ ተ ፲ ፡ ረ ፯ ፡ ድምር ፻፲፯ ይሆናል ፡ ይህም ፲ሩን ቃላተ አሪትንና ፯ቱን ቃላተ ወንጌል ያያል ፡ ፻ ያለው ፲ እንዳለው ነው ።

፳፫ኛ ፡ መዝ. ፲፰ ፡ ፩ ፡ ሰማያት ይነግራ ስብሐተእግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ ሰማያት ሲል ፯ቱን ሰማዮች ከግዕዙ ፌደል ቍጥር የተስማማ መሆኑን ማስተዋል ነው ፡ ቍ. ፯ ፡ ወው ስተ ፀሐይ ሜመ ጽላሎቶ ፡ ያለው ጌታችን በፀሐይ ፡ እመቤታችን በምሥራቅ ስለምት መሰል በፀሐይ ጥላውን (ሾመ) ሜመ አለ በግዕዙ ፌደል ሠ ፭ ፡ መ ፬ ፡ ድምር ፱ መሆ ኑን ማወቅ ነው ።

፳፬ኛ ፡ ፩ ዜና መዋ. ፳፯ ፩ የ፳ኤልም ልጆች እንዳቢቶቻቸው አለቆች የሸህና የ፻ በየክፍላቸው ንጉሡን የሚአገለግሉ በወር በወሩ የሚገቡና የሚወጡ ባ፲፪ ወሮች ሁሉ ፳፬ሽ ፳፬ሽ ፡ ባ፲፪ቱ ወሮች ፪፻፹፰ሽ እንደነበሩ ፡ ካ፩ እስከ ፲፪ ቍ. ተመልከት። ይህ ንም ለ፪ት ስትከፍለው ፻፵፬ሽ ቍ. ይመጣል ፡ ይህም ፻፵፬ ቍ. የአዳም የስሙ ቍ. ነው ። ፻፵፬ቱም በመልአኩ ክንድ ፩ድ መሆኑን ሐዋርያው ዮሐንስ በራእዩ ፳፩ ፲፯ "ወእምገ መጠነ አረፋቲሃ ፻፵፬ቱ በእመተ ሰብዕ ዘውእቱ ፩ዱ በእመተ መልአክ,, ብሎ እንደገለ ጠው ፡ ሙሴ በኦሪቱ ዘካዕበ እመት ወመንፈቀ እመት ባለው መሠረት ፡ ፪ቱ ክንድ ፪፻፲ ፳ሽ ፡ የክንድ እኩሌታ ባለው ፫፪ሽ ፡ ጥቅል ድምር ፫፻፳ሽ ይሆናል ፡ ይህም ፫፻፳ሽ ያ መቱ ቀኖች ቍጥር መሆኑን መረዳት ላስተዋይ ዋና ገንዘቡ ነው ፡ የአዳምን ስም መሠ ረትነት በግዕዙ ፌደል መሆኑን ማስተዋል ነው ።

ክፍል ፫

፳፭ኛ ፡ ምሳሌ ሰሎሞን ፳፬ ፲፭ ፡ ስብዓ ይወድቅ ጻድቅ ወስብዓ ይትነሣእ ፡ ረሲዓንሰ ይደውዩ በእኩይ ፡ ይላል ፡ ስብዓ ሲል በግዕዝ ፌደል ፡ ሰ ፯ ፡ በ ፪ ፡ ዐ ፫ ነው ፡ የሚጸፈው የፌደል ቅርጽ ከቍጥሩ ተስማምቶ የሚገኘው በኢትዮጵያ ፌደል ብቻ ነው እንጅ በማ ንም ፌደል አይገኝም ። ፯ና ፫ ቍጥር የብድር መክፈያ ጽዋዕ ማለት ነው ፡ ይህንም ለመረዳት ኦ. ዘፍጥ. ፬ ፳፬ ፡ እስመ ቃየል ተፈድየ ሀየንተ ፩ዱ ፯ተ በቀለ ፡ ላሜህሰ ይት ፈደይ ፫ወ፯ተ ፡ ያለውን ይመለከታል ፡ ለበጎም ቢሆን ለክፉ ብድር መቀበያው የ፯ት ቤት ቁጥር ነው ፡ ፌደሉና ፯ኛው ቀን ጉጦም የሚገኘው በኢትዮጵያ ፌደል ብቻ ነው ፡ ሰሎ ሞን በምሳሌው ፱ ፩ ፡ ጥበብ ሐነፀት ላቲ ቤተ ወፀቀመት ላቲ ሰብዐተ አዕማደ ፡ ፯ት ዓምዶች ያላቸው ፯ቱን ዕለታት ነው ፡ ፯ቱም ዕለታት ከግዕዙ ፌደል ደረጃ ጋራ

የተስማሙ ናቸው ፡ የማናቸውም የምሥጢር ትርጓሜ ሁሉ መሠረት ይዘ የሚገኘው በኢትዮጵያ ፊደል ቁጥር መሆኑን ማስተዋል የተገባ ነው ።

ሽ፯ኛ ፡ አርዮስ ጥበብ በሚባል መጽሐፍ ፩ ፬ «ቀዳሚ ኩሉ ተፈጥረት ጥበብ» የሚለውን ንባብ ይዞ ወልድን በጥበብ መስሎ ወልድ ፍጡር ብሎ ቢነሣ በተሳሳተበት ፊደል ቁጥር ጥበብ ሲል በግዕዝ ፊደል ጠ ፫፬ ፡ በ ፱ ፡ በ ፱ ፡ ድምር ፫፬፲፰ ይሆናል ፡ ስለዚህ ልዑል እግዚአብሔር በረቂቅ ጥበቡ ከዓለም በፊት ክርስቲያን ፫፬፲፰ ለ ቃውንትን አስነሥቶ ጸሎተ ሃይማኖትን በ፩ድ ቃል አናግሮ አስረትቶ ያስወጣውን መርምሮ መረዳት አስፈላጊ ነው ።

ሽ፯ኛ ፡ ኢሳይያስ ፲፩ ፩ "ተወጽአ በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየንርግ ጽጌ እምጉንዱ ፡፡ ብሂል፡ በትር ሲል በግዕዝ ፊደል በ ፱ ፡ ሲሆን የእመቤታችን ስሟ ፱ ቍ. ስለሆነ እመቤታችንን በ ብሎ ጠራት ፡ የጌታችንም ስም ሰው በተባለበት ሰ ፯ ስለሆነ ፡ ባ፲ ሲበዛ ፫ ስለሆነ ጽጌ አለው ። ይህም በግዕዙ ፊደል ቍ. ጸ. ፭፬ ፡ ገ ፪፬ ፡ ድምር ፯፬ ነው ። ይኸውም ፡ ፩ኛ ፯፬ ፡ ፪ኛ ፫ ፡ ፫ኛ ሰባት ፫ቱ ፩ድ መንገድ ነው ፡ የጌታን ስም ሰን በትን ማክበር በተዉ ጊዜ ሽልን አስማርከ ፫ ዘመን እንዳቆያቸውና ፫ጠላት እንዳስገዛቸው ኢሳ. ሽ፬ ፲፩ «ትነብር ጢሮስ ፫ ዓመተ አለ» ፡ ኤርምያስም ሽ፩ ፲፩ «ወት ማስን ሑላ ምድር ወይትቀነዩ ለአረሚ ፫ ዓመተ» ብሏል ። ሰንበትን ያላከበሩ ሕጉን የሻሩ ሰዎች የሚገቡባትንም ሲኦል ይላታል ፡ ሲኦል በኢትዮጵያ ፊደል ቍ. ሰ ፯ አ ፱ ለ ፪ ድምር ፱፬ ይሆናል ፡ ይህም ፯ት ጊዜ ፯ት ነው ።

ሽ፯ኛ ፡ ዳንኤል ፱ ፪ «አነ ዳንኤል አእመርኩ በውስተ መጻሕፍት ኀልቈ ዓመታት ዘከነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ ኤርምያስ ነቢይ በዘይሜለኦ ሙስናሃ ለኢየሩሳሌም» አለ ፫ ዓመት ብሎ ስለ ፫ው ዓመት ዝመረና በሽ፩ ቍ. መጽአ ብዕሰ ገብርኤል አለ ፡ ብዕሰ ገብርኤል ሲል ዐ በፊደል ቍጥር ፫ ስለሆነ የ፫ን ምሥጢር ለማሳየት ሰፈልግ ብዕሰ ገብርኤል መጣ አለ ፡ ገብርኤል ሰው ተመስሎ ለናቡከደነፆር ተገልጸለት እንደነበረ ዳንኤል ፫ ሽ፩ ... እነሆ እኔ ፬ት የተፈቱ ሰዎች አያለሁ በእሳቱ መካከል ይመላለሳሉ ምንም አልነካቸውም ያ፬ኛውም መልክ የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል ብሎ የተናገረውን ማየት ነው ። ስለ ዋናው ምሥጢር ግን ዳን. ፱ ሽ፬ ሕዝበችሁን እስከ ፫ ሱባዔ አቆያቸው በተቀደሰች አገርህ ላይ ዓመፃ ይክለከል ዘንድ ያለው የሱባዔው መንገድ ተቃንቶ የሚገኘው በኢትዮጵያ ፊደል በግዕዝ ነው ፡ ማለት የዘመኑ ቁጥር የሚሄደው እንደ ዕለታቱ ቍጥር ፡ እኑድን ፩ድ ፡ ቀዳምን ሰባት እያለ ነው ፡ እን ደዚህ ማለቱ እንደዛሬው ዘመን አቈጣጠር ከሰንበት ሱባዔ እንደወጣው ማለቴ አይ ደለም ፡ አንደ ጥንታዊው የኢትዮጵያ አቈጣጠር ሰባቱ ዓመቶች በሰባቱ ዕለታት እን ደሚብቱ ማለቴ ነው እንጂ ። የዛሬው ሱባዔ ከሰንበት ሱባዔ የወጣ ነው ማለቱም የዛ ሬው አቈጣጠር መጋቢት ሽ፱ ቀን ዓለም ተፈጠረ ይላል ። በዚህ ሐሳብ ሰኞ መጋቢት ፴ ፡ ማክሰኞ ሚያዝያ ፩ድ ፡ ረቡዕ ፪ ፡ ሐሙስ ፫ ፡ ዓርብ ፬ ፡ ቀዳም ፭ ፡ እኑድ ፮ ፡ ሰኞ

፣ እያሉ በዚህ መሠረት በእኑድ ፋንታ ማክሰኞን ፩ድ፣ በቀዳም ፋንታ ሰኞን ሰባት እያለ ጥንተ በዓላቱን ከበታቸው የሚያፋልሰውን አቄጣጠር ማለቱ አይደለም። በጥንታዊው በኢትዮጵያዊው መሠረት ሚያዝያ ፩ድ፣ እኑድን ፩ድ፣ ቀዳምን ሰባት በማለት ነው። ኢትዮጵያ በዘመነ አሪት መጻሕፍተ ብሉያትን ተቀብላ ሰንበትን እያከበረችና እየቆጠረች የኖረች አምልኮተ ጣዖት የሌለባት አገር ለመሆንዋ በጎጽዋ ለህንደኬ ተፈጽሞ ይገኛል፣ ግብረ ሐዋ. ፰ ከ፳፯ እስከ ፴፱ ቍጥር ተመልከት።

፳፱ኛ፣ ዘክርያስ ፫ ፱ «ወእብነ እንተ ወሀብኩ ቅድመ ገጹ ለዮሴፅ» (ኢያሱ) ዘዲበ አሐቲ እብን ሰብዓቱ አዕይንት እሙንቱ ያለውን ሲተረጕም ኢያሱ የያዕቆብን ዘሮች ዮርዳኖስን ባሸገረ ጊዜ ከዮርዳኖስ ውስጥ ፲፪ት ድንጋዮች አስወጥቶ ለመታሰቢያ በውጫ አስቀምጦ ስለ ነበር ያንዲቱ ድንጋይ ሰባት ዓይኖች ናቸው ባለው መሠረት የ፲፪ቱ ድንጋዮች ሰባት ዓይኖች ሲሆኑ ፲፪ት ጊዜ ሰባት ፸፩ ነው፣ ይህም የ፸ ዓመቶች ወር ወይም የሰባቱ ዕለታት ሰዓት ቍጥር ነው። የ፩ዲት ድንጋይ ሰባት ዓይኖች ያለው ባ፲፪ ሐዋርያት ስብከት ሁሉ፣ በሰባቱ ዕለታት ሁሉ የእግዚአብሔር ምስጋና ባ፲፪ቱ ሰዓቶች መፈጸሙን ሲያይ ነው። በሰባቱ ቀኖች ምስጋና ለመኖሩም ቅ. ዳዊት በ፻፲፰ኛው መዝ. "ስብዓ ለዕለትየ እሴብሐከ,, ማለቱ በሰባቱ ዕለታት አመሰግንሃለሁ ማለቱ ነው እንጂ በሰባቱ ሰዓቶች ማለቱ አይደለም። ፩ድ ፩ድ ሰዎች ሰባት ጊዜ ያቶች እያሉ ጽፈው ይገኛሉ ይናገራሉም፣ በለማስተዋል ነው እንጂ በ፩ድ ቀንስ ለምንስ ጋና የተናገረው ባ፲፪ቱ ሰዓቶች መሆኑን የሚያስረዳ ነው። መዝ ፩ ፪ «ወዘሕጎ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ፣ ወይከውን ከመ ዕፅ እንተ ትክልት ኀበ ሙኀዘ ማይ እንተ ትሁብ ፍሬሃ በበጊዜሃ» ብሏል ይህም የእግዚአብሔርን ቃል በቀንና በሌት የሚጸለይ ባ፲፪ቱ ወሮች እንደምታፈራ በወንዝ ዳር የተተከለች እንጨትን ይመስላል ማለቱን ማየት ነው። ለዚሁም ድጋፍ ሐዋርያው ዮሐንስ በራእዩ ፳፪ ፪ "«ወይውኅዝ ውስተ ማእከለ መርኀባ እምለፌኒ ውእቱ ፈለግ ወእምኀ ሐከኒ ዕፀ ሕይወት፣ ወይገብር ፍሬ ፲ወ፪ተ ወይሁብ ፍሬሁ ለለ፩ዱ ወርኀ.. ያለው ዕፀ ሕይወትን ከምድር ዳር ናት አለና ወይገብር ፍሬ ፲፪ተ ያለው ፲፪ቱን ሰዓቶች ማለቱ ነው፣ ለለ፩ዱ ወርኀ ያለውም ወርና ሰዓት ፩ድ ነው። ከላይ ያንዲት ድንጋይ ሰባት ዐይኖች ያለው በሰባቱ ዕለታት የሚነገር ከአብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ስም በተቀር ሌላ የለም ሲል ነው። እብን ሲል የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ስም ነው፣ ይህም በግዕዝ ፊደል አ ብ፣ በ ፱፣ ድምር ፴፱፣ ወል ድ ሰ.ል ወ ፮፣ ለ ፪፣ ደ ፬፣ ድምር፣ ፬፮፪ በ፬፮ ውስጥ ስንት ፮ ይገኛል ፮፣ ፪ቱ ሲደመር ፲ ድምር ፶፱፣ መንፈስ ቅዱስ ሲል መ ፩፣ ነ ፶፣ ፈ ፸፩፣ ሰ ፯፣ ቀ ፻፣ ደ ፬፣ ሰ ፯፣ ድምር ፭፻፶፯ ይሆናል፣ ከ፭፻፶፯ ስንት ፮ ይገኛል ቢሉ ፹፪፣ ይህም ሁለት ጊዜ ፮ ማለት ነው። ከ፶፱ኙ ሲደመር ፲፩ ይሆናል፣ ስለዚህ ሙሴ ለእሥራኤል ውኃ ከድንጋይ አፈለቀላቸው ማለቱ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ያፈለቀ መሆኑን ለማስረዳት ከእብን አፈለቀላቸው አለ። የፈለቀውም ውኃ ቃለ እግዚአብሔር ነው፣ ስለ ድንጋዩ፣ አሪት ዘፀ ፲፯

፮ . . . «ወትዘብሎ ለኩሉሕ ወይወጽእ በውስቴቱ ማየ ወይሰቲ ሕዝብ» ይላል ፡ ማይም ቃለ እግዚአብሔር ለመሆኑ ፡ ሕዝቅኤል ፴፯ ፫ ፬ «ወዓዕደወኒ ውስተ ማይ እስከ ብርክ እስከ ሐቍ የሚለውን እይ ። ፫ኛም ፡ ፫ኛው ዕዝራ ፲፬ ፵፬ ፡ «ወተጽሕፉ በእማንቱ ፵ መዋዕል መጻሕፍት ፸ወ፬ቱ» ይላል ፡ ፸፬ ማለት በግዕዝ ፊደል ማይ መ ፬ ፡ የ ፸ ፡ ድምር ፸፬ ፡ ይሆናልና ማይን ቃለ እግዚአብሔር ሲል እንደሆነ በዚህ ይታወቃል ።

ክፍል ፬

፳፱ኛ ፡ ማቴ. ወንጌልን ሲጽፍ ልደቱን ከ፷፩ኛው ትውልድ ከአብርሃም ዠምሮ እስከ ጌታችን አደረሰው ፡ ማነኛውም ደገኛ ሥራ ሁሉ ያለቀጥር የሚሆን የለም ፡ ስለዚህ ማቴ. ፩ ፲፩ "ወትወልድ ወልደ ወትጼውዕ ስሞ ኢየሱስሃ,, ያለውን ጌታችን የአዳምን ፍዳ ለመቀበል የአዳም ባለጋራ ዲያብሎስ አዳም በተፈጠረ በሰባት ዓመቱ ባ፩ድ ጽዋ በዕፀ በለስ ተሠውሎ ከርስቱ ከገነት ስለነቀለው ፡ ጌታችን በአዳም ስም የመጠራቱ መረጃ መልአኩ ኢየሱስ በሉት ብሎ ተናገረ ። ኢየሱስ ሲል በኢትዮጵያ ፊደል አ ፵ ፡ የ ፸ ፡ ሰ ፯ ፡ ሰ ፯ ፡ ድምር ፪፵፬ት ይሆናል ፤ ይህም ከላይ እንደተመለከተው የአዳም የስሙ ቍጥር ነው ፡ አዳምን ኤዶም ገነት አገባው ማለቱ የጌታ ሥራ ሁሉ በምሥጢር የተያያዘ መሆኑን ሲያስረዳ ኤዶም ሲል ፡ በግዕዝ ፊደል አ ፵ ፡ ደ ፬ ፡ መ ፬ ፡ ድምር ፪፵፬ ነው ። ስለዚህ ባ፩ድ ጽዋ ቢመጣበት ጌታችን ባ፷፪ ጽዋ መጣበት ፡ ይህም ፷ሽ ፷፪ን ለ፲፩ድ ስትመድበው ፷፪ ይሆናል ፡ ባ፷፪ ጽዋ የተባለ ስለዚህ ነው ። ፪ኛም አዳምን በዕለተ ዓርብ በዕፀ በለስ ምክንያት ቢያወጣው ጌታችንም በዕለተ ዓርብ በዕንጨት ተሰቅሎ ወደበታው መልሶታል። በግዕዙ ፊደል ቁ. መሠረት የቁጥሩ ትርጓሜ ልክ ሆኖ ይገኛል ፡ በሌሎቹ ግን የቁጥሩ ትርጓሜ ስለማይታወቅ ኤዶምን ኤደን ብለው ፊደሉን መን በነ ለውጠውት ይገኛል ። እንዲሁም ኢየሱስ የሚለውን አ ን ትተው የሱስ ይሉታል ፡ ይህን ሁሉ ጥን ቃቄ አያስቡትም ።

፴ኛ ፡ ማ. ፭ ፲፰ «አማን እብለክሙ እስከ አመ የኀልፍ ሰማይ ወምድር የውጣ እንተ አሐቲ ቅርጸታ» ያለው ሲተረጐም የውጣ ያለው የ በእብራይስጡ ፊደል ፲ኛ ስለሆነ ነው ፡ እንተ አሐቲ ቅርጸታ ያለው ፲ ቁ. ቅጥልና እንጥልጥል የሌለበት መሆኑን ሲያስረዳ ነው ፡ ፲ቱ ቃላት ለመሆኑም «ዘኬ ፈትሐ አሐተ እምእላ ትእዛዛት» ያለው ያስረዳል እንግዲህ የፊደል ቁ. ትርጓሜ የለም የሚሉ ሰዎች የወንጌልን ቃል የሚቃወሙ መሆናቸውን መዘንጋት አይገባቸውም ።

፴፩ኛ ማቴ. ፲፫ ፭፰ "ወይቤሎሙ ብእሲ ፀራዊ ገብረ ዘንተ,, ያለው ሲተረጐም በግዕዙ ፊደል ፀ ፯፻ ፡ ረ ፪ ፡ ወ ፮ ፡ ድምር ፯፻፮፯ ይሆናል ፡ ይህም ሐዋርያ ዮሐንስ በራዕዩ ፲፫ ፲፰ «ወዘሰ ጠቢብ ውእቱ ወዘበ ልብ ያእምር ኁላቄሁ ለውእቱ ዓርዌ እስመ አምጣነ እጓለ እመሕያው ውእቱ ወኁላቄሁኒ ፮፻፮፯ወ፮ቱ» ያለው ሲተረጐም ማቴዎስ ብእሲ ፀራዊ ብሎ ሠውሮ የተወውን ዮሐንስ በሰፊው ትእምርተ ስሙ እያለ ገልጾ አስ

ስረዳ፡ የስሙ ቁጥር ከበላዩ ፲፯ ቀኑ ትእምርተ ስሙ ለውእቱ አርዌ ብሎ አው ዘጎልቈ ስሙ የስሙ ቁጥር ያለውን ማስተዋል ነው ፡ የፊደል ቍጥር ትርጓሜ የለም ለሚሉ ሰዎች ይህ ይበቃቸዋል ።

ፀ፪ኛ ፡ ማቴ. ፮ ፱ «ከመገዘኬ ጸልዩ አንትሙሰ አቡነ ዘበሰማያት» ሲል ፡ አቡነ ማለት በግዕዝ ፊደል አ ፣ በ ፱ ፡ ነ ፡ ድምር ፲፱ ፤ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ስም ስለሆነ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስን በምሥጢር ሲአመለክት ነው ፡ ይህንንም ሐዋርያው ዮሐንስ በራዕዩ ፲፩ ፩ «ወእምገዘ ቆመ ዝክቱ በግዕ ላዕለ ደብረ ጽዮን« አለ ። በግዕ ሲል ጌታን ሰብዕ ሲል መሆኑን ዕ የሚለውን ፊደል ማስተዋል ነው ። ከርሱም ጋራ ፱፯ ፬ሺ በግምባራቸው የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ስም የተጻፈባቸው ማለቱ በአዳም ስም ቁጥር ልክ ፱፯፬ በቀን አቡነ ዘበሰማያት የሚደግሙትን ማለቱ ነው ፡ በቀን ፱፯፬ት ቁጥር እንደምን ይገኛል ብሎ ለሚጠይቅ ፡ በ፩ድ ሰዓት ፮ ደቂቅ አለ ፡ ፮ውን ለ፩ት ስትመድበው ፲፪ት ይሆናል ። ፪ኛ ከ፪ኛው ሰዓትም እንደዚህ ፲፪ት ይገኛል ፡ በዚህ ሒሳብ ካ፲፪ቱ ሰዓቶች ፲፪ት ጊዜ ፲፪ት ስለሚገኝ ፡ በየሰዓቶቹ ፲፪ ፲፪ አቡነ ዘበሰማያት የታዘዘ መሆኑን በመረዳት ፡ ጥንታውያን አባቶቻችን ባ፲፪ቱ ሰዓቶች ፲፪ ፲፪ት አቡነ ዘበሰማያት የመጸለይ ልማድ አስቀምጠውልን ስለሄዱ ፡ ዛሬም ብዙዎች ክርስቲያን ሰዎች አቡነ ዘበሰማያትን በቀን በቀኑ በአዳም በስሙ ቁጥር ልክ ሲጸልዩ ይገኛሉ ። ስለዚህ ዮሐንስ በራ. ፯ ፬ "ወሰማዕኩ ጎልቆሙ ለእለ ተኀትሙ ፲ቱ ወ፬ቱ ፻ ወ፵፬ ፡ የሚለው ከላይ እንደተመለከተው ፡ ባ፲፪ቱ ሰዓቶች ፲፪ ፲፪ት አቡነ ዘበሰማያት የሚደግሙትን ማለት መሆኑን መገንዘብ ነው ። ከላይ ባ፲፪ቱ ሰዓቶች ውሥጥ ፲፪ ጊዜ ፲፪ት ፱፵፬ት ቁጥር አለ ተብሎ እንደተጻፈው በዚህም ከ፩ ቁ. ዠምሮ እስከ ፱ ቁጥር ካ፲፪ቱ ነገደ ፭ዔል ፊታቸውን የታተሙ ስሙ የተጻፈባቸው የሚለው የአዳምን ስም ፱፵፬ትን በሺ አብዝቶ ነው ፡ ሕዝቅኤል ፱ ፬ እይ ። ስለምን የአዳምን ስም በሺ አበዛው ቢሉ ፡ አሪት ዘፀ. ፳ ፮ "ወእገብር ምሕረተ ለለ፲፻ ትውልድ ለእለ ያፈቅሩኒ ወትእዛዝየ ለእለ የዓቅቡ,, ያለውንና አሪት ዘዳግም ፮ ፲ «ወእገብር ምሕረተ እስከ እልፍ ትውልድ ለእለ ያፈቅሩኒ» ያለውን ይመልከት ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ፊደል የምሥጢረ እግዚአብሔር መነጋገሪያ መሆኑን ተገንዝበ ለልውል እግዚአብሔር ሰፊ ምስጋና በማቅረብ ፈንታ እንዳያውም ፊደላችን ከዓረብ አገር የመጣ ነው የፊደል ደረጃዎችንም ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያደራጀ አባ ሰላማ ነው ፡ ኢትዮጵያን ከአምልኮተ ጣዖት ያወጣ አባ ሰላማ ነው እያሉ ሐሰት የተጐናጸፈ ፖለቲካቸውን ሲጽፉ ይገኛሉ ፡ ኢትዮጵያ ጣዖት ታመልክለች የሚል ተጽፎበት አይገኝም ። በሰሎሞን ጊዜ መጻሕፍተ ብሉያትንና ከህናቱ ጽላተ ኪዳንን ይዘው መጥተው ሲኖሩ ፡ ጌታችን በተወለደ ጊዜ ባጼ ባዜን ዘመነ መንግሥት ሊቀ ከህናቱ አክን ፡ በአብርሃና በአጽብሐም ጊዜ ሊቀ ከህናቱ እንበረም ፍሬ ምናጦስን ግዕዝ ያስተማረው ነበር ። የኢትዮጵያ መጻሕፍት በዓለም እርሻ ላይ ተዘርተው የታሪክ አበባና ፍሬ ለቁም ነገረኞቹ ሊቃውንት ከመጠን ያለፈ በየሰዓቶቹ አደራጅቶ ሲገኝ የውጭ አገር ፕሮፓጋንዳ ባልደረቦች ዓይን በሌለው ፖለቲክ እየተመሩ ገለባ ፖለቲካቸውን ሲዘሩ ይታያሉ ። ይህን ሁሉ የውሸት

ጽሑፍ፡ የመንፈሳዊ ልብስ ለብሰው ሲሰብኩ የሚገኙ የዓለም ቤተ ክርስቲያን የተቀበለች ውና በኢትዮጵያ የሚገኙ፡ መጻሕፍተ ብሉያት የተለያዩ መሆናቸውን ከለማወቃቸው የተነሳ ነው እንጂ አውቀውትስ ቢሆን ስንኳንስ በጽሑፍ በቃል እንኳ ባልተናገሩም ነበር ። የኢትዮጵያ መንግሥትና ቋንቋ ከኖኅ ለካም ፡ ከካም ወደ ኩሳ ፡ ከኩሳ ወደ ኢትዮጲስ የመጣ ነው ፡ ካም ወደ አፍሪቃ የመጣ በ፪ሽ፯፻፯ ዓመተ ዓለም ላይ ነው ፡ ካም ግዕዝን ይዘ የመጣ የቋንቋ መለያየት ሳይሆን የባቢሎን ግምብ ሳይፈርስ ነው ።

ክፍል ፫

፴፫ኛ፡ ወንጌል ሲል በግዕዝ ፌደል ወጌ፡ ነ ፴፡ ገ ፬፬፡ ለ ፬፡ ድምር ፬፬፯፯፬፡ ከ፬፬፯፯ ስንት ፭ ይገኛል ፲፬፡ ስንት ፲ ይገኛል ፭፬፡ ስንት ፫ ይገኛል ፬፯፡ ድምር ፯፬ ይሆናል፡ ይህም በ፯፬ኙ ነገደ መላእክት ልክ መሆኑንና ኅቡእ ስሙ ፡ በግዕዝ ጎ ፭ ፡ በ ፬ ፡ ወ ፍ ፡ ድምር ፯፬ ይሆናል ዋጌታ ስም መሆኑን መረዳት ነው ። ይህን መሠረት በመከተል ዛሬ የእስላም ሽሆች እንኳ መቁጠሪያቸውን ፯፬ አድርገው ይገኛሉ ። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም የወንጌልን ቃል ፯፬ኝን በ፬ አብዝተው ፬ሽ ፬፬ ቁጥር ሰጥተውት ይገኛሉ ፡ በቅዱስ ወንጌልም የሥላሴ ፫ነት በሰፊው የተገለጸበት ስለሆነ ፡ በወንጌሉ ውሥጥ ፫ ዓይነት ቁጥር አድርገው በታል ፡ ይህም ፩ኛ ዐቢይ ምዕራፍ ፡ ፪ኛ ክፍል ፡ ፫ኛ የቃል ተራ ቁጥር ነው ። ቁጥር አርእስት ያለው መሆኑን ለመረዳት በሚትር ውሥጥ ፫ት ዓይነት ቁ. እንዳለ መረዳት ነው ። ፲፪ቱን ሐዋርያት ለዓለም አስተምሩ ሲል ዓለም ፲፪ት አህጉር መሆንዋን መገን ዘብ ይገባል ማለት የዓለም ክፍል መሠረቶች ፫ት ስለሆኑ ። ፫ቱ ባ፬ት ሲበዛ ፲፪ት ይሆናል ፡ ስለዚህ ባ፲፪ቱ አህጉረ ዓለም ፲፪ት ነገደ ጴኤል ፡ ፲፪ት ሐዋርያት ፡ ፲፪ት ነገደ መላእክት ፡ ፲፪ት ከዋክብት ፡ ፲፪ት ወሮች ፡ ፲፪ት ሰዓቶች ፡ እነዚህን ሁሉ በማስተባበር በዓለም ላይ ያመለክታል ።

፴፬ኛ ፡ ስለ ግዕዝ ምሥጢር ፡ ግዕዝ ማለት ዕለተ እኁድ መሆንዋን ማወቅና መረዳት ስለሚገባን ፡ አስቀድሞ ዕለትና ዓመት ተባባሪ ኅብር (፩) መሆኑን ለማስተዋል በቀን ፲፪ ሰዓቶች እንዳሉ ፡ በዓመትም ፲፪ት ወሮች አሉ ። እንግዲህ ሙሴ የጸፈልንን ስንመለከት በዕለትና ባመት የሰንበትን ሱባዔ የቈጠረበትን እናገኛለን ፡ የዕለቱ ቁ. ኦሪት ዘዳ. ፲፭ ፱ «ወትኤልቀ ለከ ሰብዑ ሰናብተ እምዘ አኀዝከ ትዕጽድ አመ ማዕረር» ይላል ፡ እንዘ ትኤልቀ ሰብዑ ሰናብተ ያለው ሐተታ ያዝመራ ጊዜ የሚለው ፡ ሚያዝያ ነው ፡ የቀን መሆኑንም ማጨድ ከጀመርክበት ይዘህ ሰባት ሰንበቶች ቁጠር ያለው ከሚያዝያ ፩ እኁድ ዠምሮ እስከ ግንበት ፲፱ ዕለተ ቀዳም ነው ፡ ዕለታቱን ሲደመሩ ፵፱ ናቸው ፡ ለ፯ት ሲመደቡ ፯ ፯ ይደርሳል ። ስለዚህ ሰባት ሰንበቶች ቁጠር አለና ፡ ፲፫ "ወትገብር ለከ በዓለ መጸለት ሰቡዓ ዕለተ,, ያለው ፱ኛዋን በዓለ ጰንጠቆስጤ ዕለተ እኁድን ነው ። ይህንም ለማበርታት አ. ዘሌዋ. ፳፫ ፲፩ "ወትኤልቀ እምሳኒታ ሰንበት ወእምይእቲ ዕለት እንተ ባቲ አባእክሙ ውእተ ከላስስተ ዘይሠርው ሰቡዐ ሰንበተ ትኤልቁ ፍጹመ,, ያለው ከሰንበት ማግሥት ያለ እኁድን ነው ፡ ነዶዎችን ከገበችሁበት ገሥራችሁ ቁጠ

ሩ ያለው፡ዕለተ እኁድ የምትከበረው በ፱ በ፱ኛው ቀን እንጂ በሌላ ጊዜ እንደዛሬው ዘወትር ትከብር ነበር ማለት አለመሆኑን ነዶ ካገባችሁበት ያለው ያስረዳል ። ፱ኛዋ ቀን እኁድ ትከበር እንደነበረ ለመረዳት ቁ. ፲፮ "እስከ ሳኒታ ለደኃሪት ሰንበት ትኄልቁ ፱ ዕለተ ወታበውኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር„ ያለውን መመልከት ነው ። የመዠመሪ ያው ወር እኁድ ሲጠት በ፪ኛው ወር ግንቦት ፭ ቀን እኁድ ፱ኛ ቀን መሆኑን ማስተዋል የተገባ ነው ። ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ ሚያዝያ ፴፡ግንቦት ፭፡ድም ር ፱ ማለት እንደዚህ ነው ። ፱ን በ፯ት ስታበዛው ፫፻፱ ይሆናል ፡ ይህም ግዕዝ መሆኑን ለመረዳት በኢትዮጲስ ፊደል ገ ፪፻፡ዐ ፍ፡ዘ ፹፡ድምር ፫፻፱ ነው ፡ የሱባዔውም መንገድ ከላይ እንደተመለከተው ያመቱ ቀኖች በ፱ው ሱባዔ ሲመዘኑ፡፭ኛ ግንቦት ፭ እሁድ ፭፡፪ኛ ሐምሌ ፳ ቀን ፡ ፫ኛ ነሐሴ ፭፯ ቀን ፡ ፬ኛ ጥቅምት ፲፬ት ቀን ፡ ፭ኛ ታኅሣሥ ፫ ቀን ፡ ፮ኛ ጥር ፭፪ ቀን ፡ ፯ኛ መጋቢት ፲፩ ቀን ፡ እነዚህ ሰባቱ ዕለታት እኁድ የምትከበርባቸው በዓላት ና ቸው፡ዕለተ እኁድ ከነዚህ በተቀር በሌሎቹ ዕለታት በዘመነ አሪት አትከበርም እንደነበረ አ. ዘፀ. ፭ ፱ „ሰዱሰ ዕለተ ግበር ተግባረ በቱ ኵሎ ትካዘከ„ ያለው የጌታ ቃል ሙሴ የጻ ፈው ፯ት ቀን ያሰብከውን ሁሉ ሥራ ብሎ የተናገረው እኁድን ፩ድ ብሎ እስከ ዓርብ ማለ ቱን በመዘንጋት አይደለም ። ዕለተ እኁድን በዘመነ አሪት አትከበርም ነበር የሚሉ ብዙ ሰዎች ይገኛሉ ፡ ካለማስተዋል መሆኑን እንዲረዱ ቢፈልጉ ፩ኛ ፡ አ. ዘሌዋ. ፳፫ ፲፮ እስከ ሳኒታ ለደኃሪት ሰንበት ትኄልቁ ፱ ዕለተ ፡ ፪ኛ ፭፮ ሰቡዐ ዕለተ ታበውኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ወሳምንትኒ ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግ ዚአብሔር ። ፫ኛ ፡ ፴፱ "ወአመ ዕለተ ፲ወ፭ኡ ለወ፡ቱ ሳብዕ ወርኅ አመ ፈጸምክሙ አስተ ጋብኦ እክለ ምድርክሙ ትገብሩ በዓለ ለእግዚአብሔር ሰቡዐ ዕለተ ፡ ወዕለተ ቀዳሚት ዕረፍት ይእቲ ፡ ዕለትኒ ሳምኒት ዕረፍት ይእቲ„ ብሏል ፡ የመዠመሪያይቱ ያለው ስምን ተኛይቱ ቀን ዕረፍት ናት ያለው ዕለተ እኁድን ነው ። ለጊዜው እነዚህ መረጃዎች ይበ ቃሉ ። ከላይ ከግንቦት ፭ ቀን ዠምሮ እስከ መጋቢት ፲፩ ፡ በ፱ የተመደቡትን በዕለተ እኁድ የሚገኙትን ፯ቱን ከ፩ኛው ዓመት ሰባት በኢትዮጵያ ፊደል ደረጃ ልክ ሆነው የተገኙትን ሰባቱን ፩ድ እያልክ ስትቆጥር ፡ የ፲ሩ ዓመት ፲ ይሆንልሃል ፡ ግን ከ፲፩ድ ዓመት ሰባት ዐቢይ ሰንበት ሆኖ ፡ ፭፩ ቀን በሱባዔ ፫ ንኡስ ሰንበት ይተርፋል ። ፫ቱን ትተህ ሰባቱን ይዘህ እስከ ፲ ዓመት ሰባትን ስትቆጥር ፲ ይሆናል ፡ በዚህ ሒሳብ እስከ ፲ ስትቆጥር ፬፻፸ የሚለውን ቁጥር ታገኛለህ ፡ ይህንም ፬፻፸ ላ፲ር ስትመድበው ፵፱ ይ ሆናል፡ ይህም ፵፱ ቁጥር በኢትዮጲስ ፊደል በግዕዝ ቁጥር በ ፱ ፡ አ ፵ ድምር ፵፱ ይ ሆናል ይህም በግዕዙ አብ ማለት ነው ።

፬፻፸ የሚለውም ሱባዔ ትክክለኛ ለመሆኑ ማቴዎስ ፲፮ ፭፩ "ወእምዝ ቀርበ ኀቤሁ ጴጥሮስ ወይቤሎ እግዚኦ ስፍነ እመ አበሰ ላዕሌየ እኁየ እኁድግ ሶቱ እስከ ስብዕኑ አለው ። ይህም ሲተረጐም ጴጥሮስ ወደ ጌታ ቀርቦ አቤቱ ወንድሜ እኔን ቢበ ድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበልለት እስከ ሰባት ነውን ። ፭፪ አ.የሱስም አለው እስከ ሰባት አልልህም ገና ፫ውን በሰባት እንጂ ማለት ፯ ጊዜ ፲ ፬፻፸ ማለት ነው ። እስከ ዚህ ያደረሰን የዕለተ እኁድ የግዕዝ ሱባዔ መንገድ ነው ።

ክፍል ፮

፴፭ኛ፡ የኢትዮጵያ ፊደል መሠረት ጥልቅ መሆኑን ለመረዳት ራዕየ ዮሐንስ ፩ ፰ «አነ ውእቱ አልፋ ወኦ ይቤ እግዚአብሔር» ይላል። አልፋ ሲል አ ግዕዝ ፭ኛ ወኦ ሲል አ ሳብዕ ሰባተኛ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለ። እንግዲህ ይህ ንባብ ባሳየው አካሄድ አ ብለ መገሥጫያ፡ አ ብለ መጨረሻ ሆኖ የሚገኝ ከመላው ዓለም ውሥጥ ሲመረመር የማን ፊደል ይገኛል።

፴፮ኛ፡ ዮሐንስ ፩ ፩ "ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ" ያለው ቃል ሲተረጐም፡ በኢትዮጲስ ፊደል ቤግዕዝ ቁጥር ቀ ፭ ለ ፪ ድምር ፲ ይሆናል፡ ይህ ፲ ቁጥር የወልድ ስም ነው፡ አይደለም የሚል ቢኖር አሪት ፭ ፩ "ወነበበ እግዚአ ብሔር ኩሎ ዘቃለ ወይቤ" ያለውን ያስተውል፡ ቃል ብለ ፲ቱ ቃላተ አሪትን ዘርዝሮ እንደሚያመጣ ከ፪ እስከ ፲፭ ቁ. ተመልከት፡ ፪ኛ ዘዕ. ፴፬ ፳፯ «ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ጸሐፍ ለከ ዘንተ ነገረ እስመ በዝንቱ ነገር አቀውም ለከ ኪዳነ» አለ፡ ኪዳን ሲል በግዕዝ ፊደል ከ ፬፡ ደ ፬፡ ነ ፴፡ ድምር ፬፻ ይሆናል፡ ከ፬፻ ውሥጥ ስንት ፭ ይገ ኛል ቢሉ ፱ ይገኛል፡ ኪዳን ፱ መሆኑን መገንዘብ አለ። ይህም ፱ ቁጥር የመቤታችን ስም ነው፡ ለምሳሌ ማርያም ሲል መ ፵፡ ረ ፯፡ የ ፯፡ መ ፵፡ ድምር ፻፵ ይሆናል። ፻ው ለ፭ ሲመደብ ፭ ይሆናል፡ ባ፭ቱ ላይ ፵ቱ ሲጨመሩ ፱ኛ ይሆናል። ፭፭ ..... ወጸሐፈ ውስተ ጽላት ዘንተ ነገረ ፲ተ ቃለ ይላል፡ ፲ተ ሲል ተ በግዕዝ ፊደል ፲ መሆኑን፡ ቃለ ሲልም ቀ ፭ ለ ፪፡ ድምር ፲ ይሆናልና ፲ና ቃል አንድ ነው።

፴፯ኛ፡ መንፈስ ቅዱስ ሲል በኢትዮጲስ ፊደል መ ፵፡ ነ ፴፡ ፈ ፯፻፡ ሰ ፯፡ ቀ ፭፡ የ ፻፡ ሰ ፯፡ ድምር ፭፻፻፯፭ ይሆናል፡ ፭፻ ቁጥር ዋና መሠረታዊ ምሥጢር ያለው መሆኑን የሚስረዳ የግዕዝ ምሥጢር ወደኋላ ይመጣል፡ የግዕዙ ፊደል ቁጥር ጠቅላ ላው ፭ሽ፭፻ ነው፡ ይህም ፯፭፻ ማለት ነው፡ ፭ሽ ፭፻ን ለ፯ት ስትመድበው ፭፻ ይሆናል፡ መንፈስ ቅዱስ ሲል ቁጥሩ የግዕዝ ቤት መሆኑ ነው፡ ግዕዝ ነፃነት ነፃነትም ዕረፍት መሆ ኑን መገንዘብ ነው። መንፈስ ቅዱስ ፭ ቁ. መሆኑን ለመረዳት ፭፻፻፯፭ቱን ለ፭ ሲመድ በት ፴፪ ሆኖ ፲፭ ይተርፋል፡ ፴፪ ቁ. ሁለት ጊዜ ፭ ማለት ነው። ስለዚህ ሉቃስ ፭፬ ፴፱ "ወናሁ እፈኑ ተስፋሁ ለአቡየ ላዕሌክሙ ወአንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም" ብሏል፡ ኃይለ ሲል ኀ በግዕዝ ፊደል ፭ ቁጥር ስለ ሆነ ነው።

፴፰ኛ፡ ማቴዎስ ፭፭ ፳ ስለ ቅዱስ ሥጋውና ደሙ በእንተ ሥርዓተ ምሥጢር ይላል፡ ምሥጢር ሲል መ ፵፡ ሠ ፸፡ ጠ ፫፻፡ ረ ፯፡ ድምር ፫፻፸፭ ይሆናል፡ ፫፻ው ለ፸፭ ስት መድበው ልክ ፭ያ ይሆናል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ስለሆነ ምሥጢር ያለውን ፭ ቁ. መሆኑን መገንዘብ ነው።

፴፱ኛ፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ፱፫ ፯ ... መጽአ ይጠባሕ ከመ በግዕ፡ ያለው ፈ፦ውን ዐ ሲፈ ልግ ነው፡ መጥምቁ ዮሐንስም ፩ ፳፱ ወአመ ሳኒታ ርእዮ ዮሐንስ ለኢየሱስ እንዘ ይመ

ጽእ ነቤሁ ይቤ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያአትት ኃጢአተ ዓለም፡ ያለው እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ተገኝቶ መከራ ተቀብሎ ዓለምን ማዳኑን ሲአመለክት ሰብዕ ተብሎ ከሚጠራበት ፊደሎች በግዕ ብሎ የእብራይስጡና የግዕዙ ፊደሎች ቁጥር የሚተባበሩበትን ወን ፎውን ፊደል የሰጠው በከንቱ አይደለም ።

ሻኛ ወደ ጠለቀው ምሥጢር ለመጓዝ ያሰበ አስቀድሞ የፊደሎችን መሠረት ቁጥሩን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት ፡ ይኸውና የእብራይስጥም ፊደሎች ቁጥር አላቸው ፡ አርእስተ ፊደሎቹም ፭፪ ናቸው ፡ ይኸውም ከ፭፪ቱ ስነ ፍጥረቶች የተባበሩ ናቸው ፡ ደረጃቸውም ፭ት ነው ፡ ይህንም መሠረት ተከትሎ ሙሴ ፭ቱን ብሔረ አሪት ጽፎልናል ፤ ፪ኛም ቅዱስ ዳዊት የጻፈው መዝሙር ፭ት ክፍል ይገኝበታል ፡ የእጅና የእግራችን ጣት ፭ ፭ት ሆኖ መገኘቱ ዋና ምሳሌ ነው ። ፫ኛም ዋናው መረጃ በጨረቃ በፀሐይና በከዋክብት ቁጥር የተገመረ ፭ኛውን ቀን ፩ድ ብሎ ነው ፡ በዚህ ቁጥር ዛሬ ስለማይሠራበት ነው እንጂ የሌሊትና የመዓልት የቁጥሩ መገኛ ሄኖክ በጻፈው መሠረት ጽልመት ፩ድ ብሎ ከገመረበት ፭ኛውን ቀን ፩ድ ብሎ መሆኑን ምሥጢሩ በሰፊው በኋላ ይመጣል ።

ሻ፩ኛ ፡ የግዕዝና የእብራይስጥ ፊደሎች ምሥጢር ሲመረመር የግዕዝ ፊደል ከሰባቱ ዕለታት እየተስማማ ፲፪ን አውራጎችና የሰንበትን ሰብዔዎች እየጠበቀ በፀሐይ ስፍር ኄኖክ በሚጠቱ ብርሃናት እንደጻፈው ፀሐይ በምሥራቅ ፭ት መሳክው ፡ በምዕራብ ፭ መሳክው እንደምትመላለስ ጽፎልናል ። ስለዚህ የግዕዝ ፊደሎች አርእስት ፭፭ ነው ፡ ፰፭ትን በ፭ት ስታበዛው ፪፻፪ ይሆናል ፡ በምሥራቅ ባሉት በ፭ቱ መስኩቶች ፪፻፪ ቀኖች ይገኛሉ ፡ መስኩቶች ያለው ወሮችን ማለቱ ነው ። ይህም እንደዚህ ነው ፡ ዓለም የተፈጠረ ሚያዝያ ፩ድ በዕለተ እኑድ ስለሆነ ፡ ሚያዝያ ፴ ብተቱ እኑድ ፡ ፪ኛ ፡ ግንቦት ፴፩ ብተቱ ማክሰኞ ፡ ፫ኛ ፡ ሰኔ ፴፩ ብተቱ ሐሙስ ሆኖ የቀኖች ድምር ፯፩ ይሆናል ። ፬ኛ ፡ ሐምሌ ፴ ብተቱ እኑድ ፡ ፭ኛ ፡ ነሐሴ ፴ ብተቱ ማክሰኞ ፡ ፮ኛ ፡ መስከረም ፴፩ ብተቱ ሐሙስ ፡ የዕለታቱ ድምር ፯፩ ሆኖ ፡ ጠቅላላው የ፭ቱ መስኩቶች ወይም ወሮች ፪፻፪ ይሆናል ፡ ይህ ፪፻፪ ቁጥር የግዕዝን ፊደላትና ዕለታትን አስተባብሮ ይገኛል ። ይህ ተስማምቶ የሚገኘው በምሥራቅ ሲሆን ፡ ይህ በምሥራቅ ተስማምቶ የተገኘው ቁጥር (ፊደል) ወይም ቁጥሩ በፊደል ጎብር ሆኖ መገኘቱ የታመነ ሲሆን ፡ ምሥራቅና ምዕራብ ተወራራሽ መሆናቸውን አስገነዝባለሁ ፡ ምሳሌውንም በዚህ አሳያለሁ ።

ምሥራቅ - ሀ	እኑድ	ሀ-ምዕራብ
ምሥራቅ - ሁ	ሰኑይ	ሁ-ምዕራብ
ምሥራቅ - ሂ	ሠሉስ	ሂ-ምዕራብ

በዚህ ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በምሥራቅ ፊደሎችና ዕለታቱ ፪፻፪ ፡ በምዕራብም ፊደሎችና ዕለታቱ ፪፻፪ ሲሆኑ ድምር ፫፻፭ ይሆናሉ ፡ በዕለት በፀሐይ ስፍር ሲቆጠሩ ያመቱ ቀኖች እነዚህ ፫፻፭ ብቻ ናቸው ፡ ለዚህ መረጃ ኄኖክ የጻፈውን ሚጠቱ ብርሃናትና ሙሴ በጻፈው ኩፋሌ ፯ ምዕ. እስከ ፴ ምዕ. ይመለከቷል ። ፫፻፭ትን ለ፯ት

ስትመድበው ፱፪ት ይገኛል ፡ እንደዚሁ ከ፯ቱ ዓመቶች ፱፪ ፱፪ት ሰንበት አውጥተህ ስትደምረው ፫፻፷፬ት ይሆናል ፡ ይህም ከ፯ቱ ዓመቶች ተጠራቅሞ የተገኘ ፫፻፷፬ት ቁጥር ፩ድ ንኡስ ሰንበት ይባላል ። እንደዚሁ እስከ ፵፱ ዓመት ሲቆጥሩ ፯ት ንኡስ ሰንበቶች ይገኛሉ ፡ እንደገና ከነዚሁ ከ፯ቱ ንኡስ ሰንበቶች ፱፪ ፱፪ት አውጥተህ ፡ (አውጥተህ ስል በሰባት መድበህ ማለቱ ነው) ከሰባቱ ንኡስ ሰንበቶች የወጣውን ፱፪ት ስትደምረው ፫፻፷፬ት ይሆናል ፡ ይህችም ፱ኛዋ ዓመት ዓመተ ኅድገት ትባላለች ፡ የምትከበረውም ዓመት ነው ። አሪት ዘሌ ፳፭ "ወትኄልቍ ለከ ሰብዓተ ዓረፍተ ፡ ለከ ሲል የፊደሉ ቁጥር ለ ፪ ፡ ከ ፱ ፡ ድምር ፱፪ መሆኑን አስተውል ፡ ሰብዓተ ዓረፍተ ዘሰብዓቱ ዓመት ዘምስብሚት ፡ ይላል ከ፵፱ኙ ዓመቶች ፱፪ ፱፪ እያወጣህ ሰብዓተ ዓረፍተ ባለው ሰባት ዓመቶች አድርግ ማለቱ ነው ። ደግሞ «ወእምዝ ትሬሲ ለከ ሰብዓተ ሰናብተ በበ፵ወ፱ ዓመት» ያለውን ማስተዋል አለ ። «ወቀድስዋ ለይእቲ ዓመት ዘ፱ ኵላ ዓመታ» ያለውን ፲፩ ምዕ. እይ ። ፪ኛ ኦ. ዘዳግም ፲፮ ፱ ወትኄልቍ ለከ ሲል ለከ ያለውን እንደላይኛው ፡ ሰቡዑ ሰናብት እምዘ አኀዝከ ትዕጽድ አመ ማዕረር ወትእኀዝ ትኄልቍ ሰብዑ ሰንበተ አለ ፡ ሰብዑ ሰንበተ ያለውን ከ፵፱ኙ ዓመት የሚወጡትን ሰባቱን ንዑስ ሰንበቶች ማለቱ ነው ፡ የሰንበትን ሱባዔ ነገር ዓለም ተስማምቶ ትቶታል ። እስከዚህ ያደረን የግዕዝ ፊደል ቁጥርና ደረጃ በፀሐይ እንደሚሰፈር ለማሳየት ነው ። ደግሞ ወደ እብራይስጡ ፊደልና ወደ ጨረቃ እንመለስ ።

ክፍል ፯

የእብራይስጡ ፊደል ደረጃ ፳ ነው ብየ ከላይ አመልክቻለሁ ፡ ፳፪ቱን ባፅት ሲበዛ ፻፲ ይሆናል ፡ ይህም ፻፲ ቁጥር ምሥጢር አለው ፡ ፻፲ሩ ፲ ጊዜ ፲፩ ጽዋዕ ነው ፡ ጽዋዕ ማለትም ብድር መቀበያ ማለት ነው ።

፵፩ኛ ፡ የጨረቃ መሥፈርያ ፻፳ ቁጥር አለ ይህም ፻፳ ቁጥር ለብርሃን ለብቻው ፻፳ ፡ ለጽልመትም ለብቻው ፻፳ አለው ፡ ማለት ፀሐይ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በቀን የምትጓዝበትን በሚትርና በሳንቲ-ሜትር እያከፈለ የሚያሳይ ነው ፡ ፻፳ትን ለ፯ት ስትመድበው ፲፳ ይሆናል ፡ የጨረቃ ወር የሚቆጠረው ባ፲፳ት መሆኑን መግንዘብ ነው ፡ የዚህ መግለጫ ወደፊት ይመጣል ፡ ፳ቱ የእብራይስጥ ፊደል ደረጃዎች መሠረት የጠለቀ ምሥጢር ያለው ነው ፡ ፳ን ላ፳ት ስትመድበው ፲፪ት ቁጥር ይመጣል ፡ ዛሬም የዓለም ሰዓት ሠሪዎች በሚሠሩት ሰዓት ዙሪያ ፳ ፳ ነጥብ አድርገው በዙሪያው ፳ ነጥቦች ማድረጋቸውን ማስተዋል ይጠቅማል ።

፵፪ኛ ስለ እብራዊ ፊደሎች ፡ የእብራይስጥ ፊደሎች ፳፪ ናቸው እነዚህም ፩ኛ አሌፍ ፡ ፪ኛ ቤት ፡ ፫ኛ ጋሚል ፡ ፬ኛ ዳሌጥ ፡ ፭ኛ ሄ ፡ ፮ ዋው ፡ ፯ኛ ዛይ ፡ ፰ኛ ሔት ፡ ፱ኛ ጤት ፡ ፲ኛ ዮድ ፡ ፲፩ኛ ካፍ ፡ ፲፪ኛ ላሚድ ፡ ፲፫ኛ ሚም ፡ ፲፬ኛ ኖን ፡ ፲፭ኛ ሣምኬት ፡ ፲፮ኛ ዔ ፡ ፲፯ኛ ፈ ፡ ፲፰ኛ ጻዴ ፡ ፲፱ኛ ቆፍ ፡ ፳ኛ ሬስ ፡ ፳፩ኛ ሳን ፡ ፳፪ኛ ታው ናቸው ።

በፊደል ቍጥር ፡ አሌፍ ፩ ፡ ቤት ፪ ፡ ጋሚል ፫ ፡ ዳሌጥ ፬ ፡ ሄ ፭ ፡ ዋው ፮ ፡ ዛይ ፯ ፡ ሔት ፰ ፡ ጤት ፱ ፡ ዮድ ፲ ፡ ካፍ ፳ ፡ ላሚድ ፴ ፡ ሚም ፵ ፡ ኖን ፶ ፡ ሣምኬት ፷ ፡ ዔ ፸ ፡ ፈ ፹ ፡ ጻዴ ፺ ፡ ቆፍ ፻ ፡ ሬስ ፻፩ ፡ ሳን ፫፻ ፡ ታው ፬፻ ፡ በዕብራውያን ፊደል መሠረት ቁጥሩ ይህ ነው ። ፩ድ ፩ድ ሰዎች መጻሕፍትን አስቀድመው በሰፊው ከመመርመር በፊት

ታሪክ ለመጻፍ እየቸኰሉ የፊደልን ታሪክ ለመጻፍ እየገሥሙሩ የግዕዙንና የዕብራይስጡን ፊደል ቁጥር እያዘባረቁ ጽፈውት ይገኛሉ።

ማስ፫ኛ፡ የዕብራውያንን ፊደሎችና ቁጥር ከላይ እንደተጻፈው አይደለም የሚል ቢኖር የእብራይስጡን ቅዱስ መጽሐፍ ቁጥር አስተውሎ መመርመር ነው፡ በእብራይስጥ የተጻፈው ቅዱስ መጽሐፍ ቁጥሩ በፊደል መሆኑ እርግጥ የሆነ ሲሆን፡ ከላይ የተጻፉት ፳፪ቱ ፊደላት ብቻ መሆናቸውን መረዳት የግድ ነው። በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የሚገኝውን መሠረት አልፎ ከልቡ እየፈጠረ ሚዳዊ ነገር ለወጣቶቹ ማቅረብ ከሕግ የወጣ ነው።

<u>ማ፬ኛ፡ ስለ ግዕዝ ፊደላት፡</u> የግዕዝ ፊደሎች ከእብራይስጡ የተለያዩ ናቸው ፩ኛ፡ የግዕዝ ጽሑፍ ከግራ እጅ ወደ ቀኝ እጅ ነው፡ እብራይስጡ ሲጻፍ ከቀኝ እጅ ወደ ግራ እጅ ነው፡ ፪ኛ የግዕዝ ፊደል ደረጃ ሰባት። የዕብራዊ ፊደል ደረጃ ፭ ነው። ፫ኛ፡ የግዕዝ ፊደሎች ተራ ቍጥር ፸፯ በፊደል ቍጥር ፷፪ ነው ፷፪ የተባለ የግዕዙ ፊደል ብቻ ነው። ሐተታው የሚከተለው ነው።

ክፍል ፷

ግዕዝ	አውሮፓ	ከዕብ	ሰራይ	ሣልስ	ሠሉስ	ፈጣሪ	ረቡዕ	ኃምስ	ኀሙስ	ሳድስ	ሚርብ	ሳብዕ	ቀዳም	ለሰባት ስታ ካፍለው፡
፩	ሀ	፩	ሁ	፪	ሂ	፫	ሃ	፬	ሄ	፭	ሀ	፮	ሆ	፩
፪	ለ	፪	ሉ	፬	ሊ	፮	ላ	፯	ሌ	፩	ለ	፪	ሎ	፪
፫	ሐ	፫	ሑ	፮	ሒ	፱	ሓ	፲፪	ሔ	፲፩	ሐ	፲፯	ሖ	፫
፬	መ	፬	ሙ	፯	ሚ	፲፪	ማ	፲፫	ሜ	፲፯	ም	፳፬	ሞ	፬
፭	ሠ	፭	ሡ	፩	ሢ	፲፫	ሣ	፲፯	ሤ	፳፭	ሥ	፴	ሦ	፭
፮	ረ	፮	ሩ	፲፪	ሪ	፲፬	ራ	፲፰	ሬ	፴	ር	፴፮	ሮ	፮
፯	ሰ	፯	ሱ	፲፬	ሲ	፲፭	ሳ	፲፱	ሴ	፴፩	ስ	፴፪	ሶ	፯
፰	ቀ	፰	ቁ	፲፮	ቂ	፲፯	ቃ	፳፪	ቄ	፴፫	ቅ	፴፰	ቆ	፰
፱	በ	፱	ቡ	፲፰	ቢ	፲፱	ባ	፳፩	ቤ	፴፭	ብ	፴፱	በ	፱
፲	ተ	፲	ቱ	፳	ቲ	፳	ታ	፳	ቴ	፴፱	ት	፵	ቶ	፲
፲፩	ነ	፲፩	ኑ	፳፩	ኒ	፳፪	ና	፳፭	ኔ	፵	ን	፵፫	ኖ	፳፩
፲፪	አ	፲፪	ኡ	፳፪	ኢ	፳፫	አ	፳፰	ኤ	፵፩	እ	፵፪	ኦ	፲፪
፲፫	ከ	፲፫	ኩ	፳፫	ኪ	፳፬	ካ	፳፮	ኬ	፵፪	ክ	፵፮	ኮ	፲፫
፲፬	ወ	፲፬	ዉ	፳፬	ዊ	፳፭	ዋ	፳፱	ዌ	፵፫	ው	፵፰	ዎ	፲፬
፲፭	ዐ	፲፭	ዑ	፳፭	ዒ	፳፮	ዓ	፴	ዔ	፵፬	ዕ	፵፱	ዖ	፲፭
፲፮	ዘ	፲፮	ዙ	፳፮	ዚ	፳፯	ዛ	፴፩	ዜ	፵፭	ዝ	፶	ዘ	፲፮
፲፯	የ	፲፯	ዩ	፳፯	ዪ	፳፰	ያ	፴፪	ዬ	፵፮	ይ	፶፩	ዮ	፲፯
፲፰	ደ	፲፰	ዱ	፳፰	ዲ	፳፱	ዳ	፴፫	ዴ	፵፯	ድ	፶፪	ዶ	፲፰

፳ ገ ፪፻ ጉ ፬፻ ጊ ፮፻ ጋ ፰፻ ጌ ፩ሽ ግ ፪ሽ፪፻ ጎ ፩ሽ፬፻ ፪፻
፳፩ ጠ ፫፻ ጡ ፮፻ ጢ ፺፻ ጣ ፩ሽ፪፻ ጤ ፩ሽ፭፻ ጥ ፩ሽ፰፻ ጦ ፪ሽ፩፻ ፫፻
፳፪ ጰ ፬፻ ጱ ፰፻ ጲ. ፩ሽ፪፻ ጳ ፩ሽ፮፻ ጴ ፪ሽ ጵ ፪ሽ፬፻ ጶ ፪ሽ፰፻ ፬፻
፳፫ ጸ ፭፻ ጹ ፩ሽ ጺ. ፩ሽ፭፻ ጻ ፪ሽ ጼ ፪ሽ፭፻ ጽ ፫ሽ ጾ ፫ሽ፭፻ ፭፻
፳፬ ፀ ፮፻ ፁ ፩ሽ፪፻ ፂ. ፩ሽ፰፻ ፃ ፪ሽ፬፻ ፄ ፫ሽ ፅ ፫ሽ፮፻ ፆ ፬ሽ፪፻ ፮፻
፳፭ ፈ ፯፻ ፉ ፩ሽ፬፻ ፊ ፪ሽ፩፻ ፋ ፪ሽ፰፻ ፌ ፫ሽ፭፻ ፍ ፬ሽ፪፻ ፎ ፬ሽ፬፻ ፯፻
፳፮ ፐ ፰፻ ፑ ፩ሽ፮፻ ፒ ፪ሽ፬፻ ፓ ፫ሽ፪፻ ፔ ፬ሽ ፕ ፬ሽ፰፻ ፖ ፭ሽ፮፻ ፰፻

አንባቢ ሆይ ከላይ በሰባተኛው መሥመር የተጻፈውን ቍጥር ከላይ እስከታች ሆ ሰ ባት ፡ ከታች ፦ ፩ሽ ፮፻ውን ቍጥር ለሰባት ስትመድበው ካ፩ድ እስከ ፰፻ ያለውን ቍ ጥር ተመልከት ። ፩ሽ፮፻ ቍ. የወጣው ከሰባተኛው ማለት ከሰንበት ቍ. የወጣው ፰፻ ቍጥር ትርጓሜው ዕረፍት እንደሆነ አስተውል ፡ ዕረፍትም ነፃነት መሆኑን ለመረዳት አሪት ዘፀ. ፲፪ ፴፯ ፡ "ግዕዙ ደቂቀ ፩ዔል እምራምሴ ውስተ ሰኮታ ፰፱፪ አጋር,, ያለው ሲተረጐም የእሥራዔል ልጆች በባርነት ሥራ ከሚኖሩበት ወደ ዕረፍትና ነፃነት ራም ሴ ከሚባል ሰኮታ ወደሚባል ተጓዙ ሲል ግዕዙ አለ ፡ ግዕዙ ማለት ነፃ ወጡ ማለት መ ሆኑን ለማስረዳት ፰፱፪ ብሎ አመጣው የ፰፱፪ ሐተታ ፩ዱ ፱፻ ፲ሽ. ማለት ነው ። ስለዚህ ፰፱፪ ያለው ፮፻ ሽ. ማለት ነው ፮፻ሺን ለፎ፩ ስትመድበው ፰ሺ ይሆናል ፡ ይህን ፰ሽ. ላ፲ ስትመድበው ፰፻ ይሆናል ፡ ይህም ፰፻ ቍጥር የግዕዙ ፊደል ቍጥር መሆኑ ነው ።

፪ኛ ፡ ፰፻ን ላ፲ ስትመድበው ፠ ይሆናል ፡ ፠ ቍጥር ክርስቶስ ማለት ነው ፡ ስለ ዚህ በኢትዮጵያ ፊደል ከ ፱ ፡ ረ ፮ ፡ ሰ ፯ ፡ ተ ፲ ፡ ሰ ፯ ፡ ድምር ፠ ይሆናል ። ክርስ ቶስ የዕረፍትና የነፃነት ጌታ ለመሆኑ ዳንኤል ፱ ፳፭ "ተአምር ወትሌቡ እምፀዓተ ቃሉ ዘታወሥእ ወትትሐነጽ ኢየሩሳሌም እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ሰብዓ ሰንበታት,, ያለውን ተመልከት ፡ የግዕዝ ፊደል መሠረት ለመሰርሰር የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ ይህን ታሪክ ይመልከቱ ።

፴፭ኛ ፡ በ፳፰ኛው ክፍል እንደሚአመለክተው መንፈስ ቅዱስ ሲል በፊደል ቍጥሩ ፰፻፱፯፮ ነው ። ፰፻ ቍጥር ከሰንበት ሱባዔ የወጣ መሆኑን ከላይ ተነግሯል ፡ ፱፮ትም የሰ ንበት ቍጥር ነው ፡ በግዕዙ ፊደል ሰንበት ሲል ሰ ፯ ፡ ነ ፴ ፡ በ ፱ ፡ ተ ፲ ፡ ድ ፱፮ት ይ ሆናል ፡ ፱፮ትን ለሰባት ሲመድቡት ፰ ይሆናል ፡ ፰ቱንም ለሰባት ስትመድበው አንድ ሆኖ አንድ ይተርፋል ፡ አንድ ቍጥር ዘወትር እኁድ መሆንዋን መገንዘብ ነው ። እኁ ድም ግዕዝ መሆንዋ ፡ ግዕዝም ዕረፍትና ነፃነት መሆኑን ከላይ እንደተጻፈው "ግዕዙ ደ ቂቀ እሥራዔል እምራምሴ ውስተ ሰኮታ,, ያለውን ይመለከቷል ።

፴፮ኛ ፡ ከላይ እንደተመለከተው የዕብራይስጥ ፊደሎች ተራ ቍጥር ፳፪ ፡ የግዕዝ ፊ ደሎች ተራ ቍጥር ፴፮ መሆናቸውን ማስተዋል አለ ። በዕብራይስጡ ፊደሎች የማይገኙ በግዕዙ ፊደል ውስጥ ፬ ፊደሎች አሉ ፡ እነዚህም በግዕዙ ፊደል ተራ ቍጥር ፩ኛ ኀ ፡ ፪ኛ ጎ ፡ ፱ኛ ጸ ፡ ፫ኛ ፀ ፡ ፬ኛ ፕ ፡ ና፞ው ። እነዚህ ፬ቱን ፊደሎች በዕብራይስጥ ፊደሎች ፩ድ ፩ድ ሰዎች ያለሚዛን ደባልቀዋቸው ይገኛሉ ። ጥልቁን ምሥጢር ለመመርመር

መንግሥቱንና ቋንቋውን ሲያያዝ የመጣውን ያበቶቹን ፊደልና ጽሑፍ ይዘ መጥቷል፥ ካም ወደ አፍሪቃ በመጣ ጊዜ የቋንቋ መለያየት ገና አልነበረም ፥ ካም ወደ አፍሪቃ የ መጣ ኖኅ ለቮቱ ልጆቹ ለሴም ፥ ለካም ፥ ለያፌት ፥ ዓለምን ካካፈለና ካረፈ በኋላ ነው ፥ ኖኅ ያረፈ ከማየ አይኅ በኋላ በ፫፻፶፭ ፥ በ፱፻፶፮፻፮ ዓመተ ዓለም ላይ ነው ፥ የቋንቋ መለያ የት የሆነ ኖኅ ካረፈ ከ፱፻፭፩ ዓመት በኋላ በ፱፻፷፻፭፻፷ ዓመተ ዓለም ላይ ነው ። አን ዳንድ ሰዎች የባቢሎን ግንብ እስኪፈርስ ኖኅ ካረፈ በኋላ ፱፻፭፩ ዘመን ወደርስቱ ሳይ ሄድ እዚያው ኖረ እያሉ መሠረት የሌለው ጽሑፋቸውን ሲጽፉ ይገኛሉ ፥ የካም ፬ኛው ልጁ ከነዓን ወደ አፍሪቃ አልሄድም ብሎ ካበቶቹ ፊቃድ ወጥቶ የሴምን አገር ይዘ እሥራዔል ከግብጽ እስኪወጡ ድረስ እንደቆየ መጻሕፍት ይነግሩናል ። ካም ፫ት ልጆቹን ይዘ ወደ አፍሪቃ አልመጣም የሚል ቢኖር ኩሩሌ ፲፩ ፲፫ "ወከፈለ ካም ለወሉዱ ወወ ጽአ መክፈልት ቀዳሚ ለኩሳ መንገለ ጽባሕ ፥ ወኅረበ፣ሃ ለምሥጻሬም ፥ ወኅረበ፣ሁ ሎቱ ለፉድ ፥ ወኅረበ፣ሁ ለከነዓን መንገለ ዓረበ ባሕር" ፥ ካም ላ፬ቱ ልጆቹ እንዳካፈለ ፥ ከነዓን ወደአፍሪቃ አልመጣም ብሎ የሴምን አገር ይዘ እንደ ቀረ ኩሩ. ፲፪ ፲፱ "ኢትጎድር ውስተ ምድረ ሴም እስመ ለሴም ወለውሉዱ ወጽአ አጽ ፥ ርገ-ም አንተ ወርገ-መ ትክ ውን እምኵሉ ውሉደ ኖኅ" ብሎ ካም ከነዓንን እንደረገመው ማስተዋል ነው ፥ የከነዓን ዘሮች የሸሜል ልጆች ከግብጽ እስኪወጡ ድረስ በሴም አገር አውራጃዎች ሁሉ ነግሠ ውበቸው እንደኖሩ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል ።

፱፩ኛ ፥ የኢየሩሳሌም ከህንና ንጉሥ መልከ ጼዴቅ የካም የልጅ ልጅ የከነዓን ልጅ ነው ፥ መረጃውን የፈለገ ቅ. ጳው. ዕብ. ፯ ፮ "ወለዘኢኮነሰ እምዘመዶሙ ወህበ አብርሃም ዐሥራ ተ ወውእቱ ባረከ ለአብርሃም ዘሎቱ ተስፋ" እንዳለ ዘመዳቸው ላይደለ አብርሃም ከ፲ ፭ድ ሰጠው አለ ። ይህንም ከላይ ባ፭ኛው ቁ. "ወደቂቀ ሌዊሰ ሶበ ይነሥኡ ክህ ነተ በሙ ሥርዓተ ትእዛዝ ከመ ይንሥኡ አሥራተ እምሕዝብ" የሌዊ ልጆችስ ክህ ነትን በያዙ ጊዜ ከሕዝብ ከ፲ አንድ እንዲቀበሉ ትእዛዝ አላቸው ብሏል "በከመ ሥር ዓተ ሕጎሙ እምላዕለ አኃዊሆሙ እለ ወጽኡ እምሐቌሁ ለአብርሃም" ፥ ከአብርሃም አብ ራክ እንደወጡት ከወንድሞቻቸው እንደሚቀበሉት እንደ ሕጋቸው አለ ። አንባቢ ሆይ ዘኢኮነ እምዘመዶሙ ያለውንና ፥ እምላዕለ አኃዊሆሙ ያለውን አስተውል ፥ በሴም አ ገር ብዙውን አውራጃ የካም ዘሮች ሠልጥነውበትና ነግሠውበት እንደኖሩ ቅ. መጽ ሐፍ ሲነግረን በመቀበል ፋንታ ልብ ወለድ ታሪክ እየፈጠሩ መጻፍ ከፍ ያለ ያታላይ ነት ሥራ መሆኑን ማወቅ የተገባ ነው ፥ እንደዚህ እስከማለት ያደረሰን የሴም ዘሮች ከቀዳማዊ ምኒልክ ወገኖች ሌላ ወደ ኢትዮጵያ በጦር ኃይል ገብተው የካምን ዘርአ መንግሥት አጥፍተው የራሳቸውን መንግሥት አቁመው ኢትዮጵያን አሠለጠኑ ብለው ሲጽፉ በማየቴ ነው ። ይህንንም የኢትዮጵያ ልጆች እየተቀበሉ ለመጭው ትውልድ በጽሑፍ ሲአስተላልፉ እያየሁ በተቻለኝ መጠን ወጣቶችን አስጠነቅቃለሁ ።

፱፪ኛ ፥ ስለ ኢትዮጵያ መሠረት በ፵፪ኛው ክፍል እንደተመለከተው ከኖኅ ገቦምሮ እስከ ንግሥተ ሳባ በካም ቤት የወረደው መንግሥትና ፊደል ሳይቋረጥ እንደመጣ በዙ

ዎች መረዳዎች ይገኛሉ ። ፩ኛ ስለ መንግሥቱ በራግው ዘመን፥(ራግው ማለት የፋሌቅ ልጅ ነው ፥ ፋሌቅ ማለት በዘመኑ የባቢሎን ግምብ ፈርሶ በየክፍለ ሀገራቸው ሳይሄዱ የነበሩ የኖኅ ዘሮች የተበታተኑበት ነው ።) በራግው ዘመን በ፪ሽ፷፪ ዘመን አቅራቢያ በኢትዮጵያ ሳባ የምትባል የሴት ንግሥት ነግሣ እንደነበር የቅ. ጴጥሮስ ጸሐፊ የነበረው ቀሌምንጦስ በጻፈው መጽሐፍ ይገኛል ። ፪ኛ ፥ እስራኤል በግብጽ በነበሩ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ንጉሠ ነገሥት የነበረው አዜጋን የሚባለው ስለ ወባይ ወኃ የሚገብሩትን ወርቅ ፥ ግብጻውያን ስለ ከለከሉ ፥ የግብጹ ንጉሥ ፥ ሙሴ የግብጽ ንጉሥ ልጅ ይባል በነበረ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተልከ መጥቶ ነገሩን በዕርቅ ጨርሶ የንጉሡን ልጅ አግብቶ ይዟት እንደሄደ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ የጻፍው ይገኛል ። ይህችንም ሴት ፭ኤል ወደ ምድረ ርስት ሲገቡ ሙሴ ይዟት ወደ ምድረ ርስት ሲጓዝ አይተው ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም ሙሴን ስለአሙት እግዚአብሔር ተቆጥቶ ማርያምን በለምጽ እንደቀጣት ኦሪ. ዘኍ. ፲፪ ፩-፲፪ ብትመለከት ፥ እግዚአብሔር ከኢትዮጵያውያን ጋራ መኖሩን ትረዳለህ ፥ ሙሴ በጻፈው ፭ቱ ብሔረ አሪት ኢትዮጵያ የሚለውን ሁሉ ፫ ሊቃውንት ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ ሲገለብጡ ነው ። በነሱ ቋንቋ ፀሐይ ያጠቈረው ያቃጠለው ለማለት ኢትዮጲስ እያሉ ሰየሙት እያሉ ጽፈው ይገኛሉ ፥ አስቀድመው የሰው አገር ታሪክ እናስረዳ ከማለት የራስን አገር ታሪክ ማጠናቀቅ የተሻለ ነበር ፥ አሪቱን ሙሴ የጻፈው በ፫ሽ፯፻፵፫ ዓመተ ዓለም ላይ ነው ። ተወልዶ ያደገ ግብጽ ላይ ስለሆነ ኢትዮጵያንም ራሱ ከብዙ ሠራዊት ጋራ መጥቶ ስለሚአውቃት ስሟን እየጠራ እያስተካከለ ጽፏል ። እንዳይከድም ከነምልክትዋ "ግዮን ዘየዓውዳ,, ዓባይ የሚዘርባት ብሎ በኦሪ. ዘፍ. ፪ ፲፫ የጻፈውን መመልከት ነው ፥ ታሪክ እየተባለ ተጽፎ የሚገኘውን ሁሉ ወደ ሥር ገብቶ ሳይመረምሩ እንዲሁ እያነሱ መጻፍ ምሳሌው እንደ ገደል ማሚቶ ያለ ማለት ነው ። ስለዚህ ሳይመረምሩ መጻፍ ከምስጋናው መነቀፉ የበለጠ መሆኑ መገንዘብ የተገባ ነው ።

፬፫ኛ ፥ በኢትዮጵያ ላይ ንግሥት ማክዳ ከላይ በ፬፪ኛው ክፍል በተጻፈችቱ መሠረት በኢየሩሳሌም ዳዊት ወልደ ዕሤይ በ፬ሽ ፬፪ ፵፪ ዓመተ ዓለም አቅራቢያ በነገሠ ጊዜ በፊተኛይቱ ሳባ ትባል በነበረችቱ ስም ማክዳ ንግሥተ ሳባ ተብላ ስለ ነገሠች መ. ቅዱስ በ፫ኛው ነገሥት ፲ ፩-፲፩ ፥ ፪ኛ ዜና መዋ. ፱ ፩-፲ ተመልከት ፥ ከላይ ከካም ዝርያ ሮ መንግሥቱና ፊደሉ ቋንቋው እንደመጣ እናስተውል ። አንዳንድ ሰዎች ካምን ንጉሥ አልነበረም ይላሉ ቅዱስ ዳዊት በ፤፩ኛው መዝ. ቊ. ፸፫ "ወያዕቆብኒ ኃደረ ምድረ ካም.. ያለው ይመልከት ፥ ስለ ቋንቋና ፊደልም ካም ወደ አፍሪቃ ከመጣ ዝርያው መንግሥቱ ሳይገለበጥና ቋንቋው ሳይናጥ መቈየቱን ማለት ነው ። ቋንቋውና ፊደሉ ከመንግሥቱ ጋር መኖሩን የሚያስረዳው የንግሥተ ሳባ ታሪክ ነው ፥ የንግሥተ ሳባ ታሪክ በነገሥቱና በዜና መዋዕሉ ተጽፎ እንደሚገኘው ፥ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደስ ሠራ ብሎ ታምሪን የሚባለው የነጋዴዎች ሹም ወደ በነገራት ጊዜ ፥ እግዚአብሔርን አዋቂ ስለነበረች ሄደ ለመረዳት አስባ ተነሳች ነገ. ፲ ፩ "ወንግሥተ ሳባ ሰምዓት

ስሞ ለሰሎሞን ወስሞ ለእግዚአብሔር ፡ ወመጽአት ትፍትኖ ምስለ ጥበብ፡፡ ይላል ፡ እነ ዚህ ፩ኛ ስሞ ለሰሎሞን ፡ ፪ኛ ወስሞ ለእግዚአብሔር ፤ ፫ኛ ፡ ትፍትኖ ምስለ ጥበብ የተ ባሉ ፫ቱ አርእስቶች ያልተማረ የአረመኔ ንግግሮች ናቸው ለማለት የተገባ ነው ለማለ ት የተመቸ ይሆንን ? ። ለንጉሥ ሰሎሞን ስንኳንስ የሰው ቋንቋና የእንስሳትና የአራ ዊት ቋንቋ አዋቂ ስለነበረ የጠየቀችውን ሁሉ እንደተረጐመላት ፡ ቍ. ፫ እይ ፡ የሰሎ ሞንን ጥበብና የቤተ መቅደስን ሥነ ሥርዓት አይታ እንዳደነቀችው በቁ. ፭ ፯ ፵ እይ ። እግዚአብሔርን አዋቂ እንደነበረች ዋና መረጃ ከልብዋ አስባ በቃልዋ የተናገራችው በእሥራኤል አልጋ ላይ ሊያስቀምጥህ የወደደ እግዚአብሔር ምስጉን ይሁን ብላ የተ ናገረችው ንግግር ነው ። ፪ኛም ‹ወአንገሠከ ለዕሌሆመ› ትግበር ፍትሐ ወጽድቀ ያለ ችው ንግግር የአረመኔ ቃል ነው ለማለት የሚቻል ይሆንን ። ከአሪት በፊት ሃይማ ኖት አልነበረም ለሚመስላቸው ግብዞች ከአሪት በፊት ሃይማኖት እንደነበረ ሐዋርያ ጳውሎስ ወደ ገላትያ በጻፈው መልእክቱ ፫ ፡ ፳ ‹እስመ አቅደመ ከመ በአሚን ያጸድቆሙ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ፡ አቅደመ አሰፍዎቶ ለብርሃም ከመ ቦቱ ይትባረኩ ኵሎሙ፡ አ ሕዛብ› ፡ እግዚአብሔር አሕዛብን በሃይማኖት እንዲአጸድቃቸው አስቀድሞ ለአብርሃም ተስፋ ሰጥቶት እንደነበረ ፡ በዘርህ አሕዛብ ይባረካሉ› እንዳለ ፡ በአብርሃም ዘር በሰ ሎሞን ስም መመስገኑን ያያል ፡ ፪ኛ መ. ዕብራ. ፲፩ ፩ ‹ሃይማኖትሰ ጥይቅት ይእቲ ለዘ ይሴፈዋ ሀለዉ ተሰፈዎሙ ንዋየ ዘኢያስተርኢ ፡ በተአምኖ ጎየሰ መሥዋዕተ አቤል እምዘ ቃየል ፡ በተአምኖ ፈለሰ ሄኖክ ፡ በተአምኖ አመ ነገርዎ ለኖኅ ፡ በተአምኖ ሰምዐ ዘተሰምየ አብርሃም» ብሏል ። ሃይማኖትን አስቀድሞ በተመረጡ ሰዎች እንደታወቀች ከተስፋ ጋር የመጣች መሆንዋን እንረዳ ፡ ይህን ከተረዳን በኋላ ንግሥተ ሳባ ከታላላ ቆቹ ባለተስፋዎች ፩ኛይቱ እርስዋ መሆንዋን የሚአስረዳ ማቴ ፲፪ ፵፪ «ንግሥተ አዜ ብ ትትነሣእ አመ ዕለተ ደይን ምስለ ዛ ትውልድ ወትትፋታሕ እስመ መጽአት እምአጽ ናፈ ምድር ከመ ትስማዕ ጥበቦ ለሰሎሞን ፡ ወናሁ እምሰሎሞን ዘየዐቢ ሀሎ ዝየ» (ከዚ ያች ትውልድ ጋር በፍርድ ቀን የአዜብ ንግሥት ለመፋረድ ትነሣለች ፡ የሰሎሞንን ጥ በብ ለመስማት ከመሬት ዳርቻ መጥታለችና) ብሎ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ ያለ ው ንግሥተ ሳባ ሰሎሞን የእግዚአብሔር ስም ቤተ ሠራ ባልዋት ጊዜ ለመረዳት ወደ ኢየሩሳሌም መጣች ብሎ ፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ እኔ ብመጣ አልተቀበላችሁኝም አላመ ናችሁኝም ማለቱ ነው ፡ በጌታችን አንደበት እንደዚህ የተመሰገነችቱን ንግሥት መጽሐፍና ፊደል አልነበራትም ለማለት ሲሞክሩ ለሚገኙ ሰዎች አዝናለሁ ።

፱፬ ፡ ንግሥተ ሳባ ከሰሎሞን ጋር መኃልይን ተናግራለች ፡ ፲፭ መክሊት ወርቅ እጅ መንሻ ሰጥታለች ። በ፲፭ው መክሊት ቁጥርና በመኃልይ የሚገኘውን ምሥጢር በሌላ ይገለጻል ፡ አሁን ለመግለጽ የምፈልገው የፊደልንና የመጻሕፍትን ነገር ነው ። ንግሥተ ሳባ ከሰሎሞን ከተናገረች በኋላ የመጻሕፍተ አሪትን ምሥጢር ስለተገነዘበች መጻሕ ፍተ አሪትን ከዕብራይስጥ ሊቃውንቶችዋን በግዕዝ አስገለብጣ አስመጥታለች ። መጻሕ

ፍተ ኦሪት የመጡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ካንድ ሺ በላይ ነው። ከንግሥተ ሳባ ገቢ ምሮ እስከ ዘሩባቤል በየጊዜው መጻሕፍተ ነቢያት መጥተዋል፣ በመጨረሻም መቃብ ያኑ መጥተዋል፣ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ መጻሐፍት የሚገኙ በኢትዮጵያ ሲ ሆን፣ ልዑል እግዚአበሔር በቸርነቱ ያደለንን መንፈሰ ሃብት ለማሳነስና ለመቀነስ ከተ ነሡ ሰዎች ጋር ግብረ አበር ለመሆን የኢትዮጵያን ክብር እናጐድላልን እየመሰላቸው እንዲያውም በኢትዮጵያ የቆዩትን ቀዋምያኑን መጻሕፍት በልሳንዋ ይዛ የምትገኝቱን ሀገር፣ መጻሕፍቶችዋ በዓለም ቤተ መዛግብት ምስክርነታቸውን ይዘው እየታዩ የጠላት ሰባኪ ያወራውን እየተከተሉ በኢትዮጵያ ስንኳንስ መጻሕፍተ ብሉያት በግዕዝ ተጽፈው ሲገኙ ይቆይና የፊደሎች ደረጃ ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያሉት ፊደሎች የተደ ራጁ በፍሬምናጦስ ነው እያሉ የጻፉትን የተንኮል ጽሑፍ ተቀብዩ በዛና ለወጣቶቹ እየተሰናዳ ለመጭውም ትውልድ ለመተላለፍ ዝግጁ መሆኑን ስላየሁ፣ ለሀገሬ በተቻ ለኝ መጠን የጠላትን ስብከት ለመከላከል ሕሊናዬ አስገደደኝ። መጻሕፍቱን ለመመር መር ብዙ ድካም ቢአጋጥመኝም በተቻለኝ መጠን ወደ ፊቴ መግፋት እንጂ የሰውን ብዛት ፈርቼ ወደ ኋላዬ የምመለስ አይደለሁምና የኢትዮጵያ ወጣቶች የአፍ ተቃዋሚ ድምፅ ፈርታችሁ ወይም አይታችሁ የጽሑፍን መሠረት ሳትመረምሩ በቶሎ እንዳት ጥሉት በመላው ዓለም ዋና ሆነው የሚገኙ መጻሕፍት የዓለም ቤተ ክርስቲያን በተቀ በለችው ቅዱስ መጽሐፍ መጽሐፈ ብሉያትን በ፴፱ኝ ቀኖጥር ወስነዋቸው ይገኛሉ። እነዚህ ፴፱ኝ ሆነው የተቈጠሩ መጻሕፍቶች ሳይቆናጸሉና ሳይጐድሉ ሙሉ ሆነው ተገኝተው ቢሆን፣ ከነዚህ ተለይተው በኢትዮጵያ የሚገኙት የ፲፭ መጻሕፍት መጐደል ባልሆነም ነበር። ባ፲፭ቱ መጻሕፍቶቹ ላይ በ፴፱ የተወሰኑትን ጉድለት ያላቸውን መጻ ሕፍቶች ታቅፈው፣ የአይሁድን ምክርና ፈቃድ በመከተል ከነዚህ ከ፴፱ኙ መጻሕፍተ ብሉያት በተቀር ሌላ መጽሐፍ እንዳትቀበሉ ብለው መርዝ የተመላ ምክራቸውን ከጐ ደለውና ከቀኖጽሉ መጽሐፍ ጋር ስለ ሰጡአቸው የዓለም ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ያነን አክብረው እንደተሸከሙ አሉ፣ ይህን ሸክም ከራሳቸው አውርደው በመመርመር ፋንታ የኢትዮጵያን መጻሕፍት ለመንቀፍ ሲሞክሩ ይታያሉ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ወጣቶች እንዲገነዘቡት አስቀድሜ የኢትዮጵያን መጻሕፍት ስምና ቁጥር በተርታ አመጣለሁ።

ክ ፍ ል ፲

፱ኙ፣ ፩ኛ፣ ዓለም በተፈጠረ በ፩ሺ ፱፻፺፮ ዓመተ ዓለም ሄኖክ የጻፈው መጽሐፍ።

፪ኛ፣ በ፲ሺ ፰፻፵፫ ዓመተ ዓለም እ ሥራዔል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ሙሴ ስለ ትውልድና ዘመን የጻፈው መጽ ሐፈ ኩፋሌ።

፫ኛ፣ ጥበበ ሰሎሞን

፬ኛ፣ መክብብ

፭ኛ፣ ጥበብ

፮ኛ፣ ጥበበ ሲራክ

፯ኛ፣ መጽሐፈ ጦቢት

፰ኛ፣ መጽሐፈ ዮዲት

፱ኛ፣ መጽሐፈ ባሮክ

፲ኛ ፡ ተረፈ ኤርምያስ
፲፩ኛ ፡ አርአያ መጽሐፍ ዘኤርምያስ
፲፪ኛ ፡ ፫ኛ ዕዝራ
፲፫ኛ ፡ ፬ኛ ዕዝራ
፲፬ኛ ፡ ስብሐተ ፫ቱ ደቂቅ
፲፭ኛ ፡ የሶስና ታሪክ
፲፮ኛ ፡ የቤልና የዘንዶ ታሪክ
፲፯ኛ ፡ ጸሎተ ምናሴ
፲፰ኛ ፡ ፬ቱ መቃብያን
፲፱ኛ ፡ የሚዶናውያንና የሞአባውያን ታሪክ ።

ከላይ ከተዘረዘሩት መጻሕፍት ስብሐተ ፫ቱ ደቂቅ ፡ የሶስና ታሪክን ስለ ቤልና ዘንዶው ፡ ፫ቱ ከመጽሐፈ ዳንኤል የወጡ ናቸው ።

፲፱ኙ መጻሕፍቶች የተለዩ ናቸው ።

፩ኛ ፡ መጽሐፈ ሄኖክ ማለት የመጻሕፍቱ አባት ማለት ከመሆኑ በላይ የዕለታትና የአውራጎ ፡ የዓመታትን ነገር የጻፈ ፡ ዕለታቱን በወር ፡ ወሮችን ባመት ፡ ዓመቶችን በሱባዔ ሰንበት እያደራጀ የጻፈ ፡ የፀሐይንና የጨረቃን መንገድ የጽልመትንና ፡ የብርሃንን ምሥጢር የሚአሳይ ጽልመትና ብርሃን የሚፈራረቁበትን ፻፷፭ት ቀኖጥር ለብርሃን ፡ ፻፷ ቀኖጥር ለጽልመት መሥፈሪያዎችን ያደራጀ የመጻሕፍቱ ሁሉ ምንጭ ነው ፡ እንዳን ነቅፈው ፡ ሐዋርያው ይሁዳ የያዕቆብ መንድም በመልእክቱ ፩ ፲፬ አስረድቶ ናል ፡ መጽሐፉም ሲገምር ቃለ በረከት ዘኬኖክ ብሎ ስሙን ጠርቶ ይገምራል ።

፪ኛ ፡ መ·ሴ የጻፈው ኵሩሌ "ዝንቱ ነገረ ኵሩሌ መዋዕላተ ሕግ ወስምዕ ለግብረተ ዓመታት በተሰብየቶሙ አ፡ቤላት ውስተ ኵሉ ዓመታቲ ዓለም በከመ ተናገሮ ለሙሴ በደብረ ሲና አመ ዐርገ ይንሣእ ጽላተ ዘእብን ዘሕግ ወዘ ትእዛዝ,, ብሎ በደገኛው የጻፈውን ስም ጠርቶ ይናገራል ፡ መጽሐፍም ስለ ዘመን ቍጥርና ስለ ትውልድ ስለ ስነ ፍጥረታትም በሰፊው የሚአስረዳ ምሥጢር ያለበት ነው ። ፫ኛ ፡ የሰሎሞን መጻሕፍቶች ፭ኛ ተግሣጽ ፡ ፪ኛ ጥበብ ፡ ፫ኛ መክብብ ብዙ ምክርና መንፈሳዊ ጥበብ የሚገኝባቸው ናቸው ።

፬ኛ ፡ መጽሐፈ ሲራክ ከመጻሕፍቱ ምንጭ ልዩነት የሌለው ምክሩ ሰፊ የሆነ ጥቅም የሚገኝበት ነው ።

፭ኛ ፡ ጦቢያ የጻፈው መጽሐፍ በሰፊው የአ፡የሩሳሌምን ሰዎች ክፋት እየ ዘረዘረ የሚናገር ብዙ ታሪክና ምሥጢር የሚገኝበት ነው ።

፮ኛ ፡ መጽሐፈ ዮዲት የተባለው መጽሐፍ ሜዶን ላይ ባጥና የምትባል ከተማ አርፋክስድ የተባለ የሜዶን ንጉሥ እንደምን አድርጎ እንደሠራት ይናገራል ፡ ናቡከደነፆር የሚለው የኋለኛውን አይደለም የፊተኛውን ነው ፡ የጽሑፉ አካሄድም ታሪኩ የተስማማ ነው ።

፯ኛ ፡ የባሮክም ጸሎት የሚነቀፍ አይደለም ።

፰ኛ ፡ ፫ቱ የኤርምያስ መጻሕፍቶች የአ፡የሩሳሌም ሰዎች ኤርምያስን እውነት በመናገሩ ጠልተውት ስለነበረ ነው እንጂ በመጻሕፍቱ ነቀፋ አግኝተውባቸው አይደለም ።

፱ኛ ፡ ዕዝራ የጻፋቸው ፪ መጻሕፍቶች በጣም የተመሰገኑ የማይታለፍ ምሥጢር የሚገኝባቸው ማለት የዕዝራ ዕርገት የእሥራኤልን መመለስ ለእዝራ መጻሕፍተ አሪት እንደተገለጸለት መረጃዎች የሚገኙ በነዚህ መጻሕፍቶች መሆኑን ለመረዳት ይኖው ፲፬ ፴፱ "ወፈታሕኩ አፉየ ወመጠወኒ ጽዋዐ ዘምሉእ ማየ ወጎ ብሩ እሳተ ይመስል,, ። በ፵ ቁጥር "ወነሣእኩ ወሰተይኩ ወጐሥዐ ልብየ ጥቀ ጥበበ ፡ ወከብደ ውስተ እንግድዓየ ልቡና ወመንፈስየኒ ተዓቅብ ወትዘምር,, ይላል ፡ ይህ መጻሕፍቱ እንደተገለጡለት ነው ። በቁ. ፵፰ "ወገበርኩ ከማሁ አመ ራብዕ ዓመት እምነ ሰንበታተ ዓመታት እምድኅረ ዓመተ ዙነኔ በ፱፱ አመ፲ሩ ለጽልመት በሣልስ ወርኅ ወመዋዕሊሁ ፯ወ፪ቱ ሎቱ ውእተ አሚረ ነሥእዎ ለእዝራ ብሏል ። (ነሥእዎ) ወሰዱት ማለቱ ነው ።

፲ኛ ፡ ከመጽሐፈ ዳንኤልም ፫ቱን ክፍሎች ያወጡአቸው በከንቱ ነው እንጂ ምንም ክፉ ነገር ተገኝቶባቸው አይደለም ።

፲፩ኛ ፡ ጸሎተ ምናሴ እንደዚሁ የእግዚአብሔርን መሐሪነት ለመሠወር ያሰቡት ነው እንጂ ጸያፍ ነገር የለበትም ።

፲፪ኛ ፡ ያ፬ቱ መቃብያንም ታሪክ እሥራዔል ከባቢሎን ከተመለሱ በኋላ ዘሩባቤልን አንግሠው ቤተ መቅደስን አድሰው ከዚያ በኋላ የተደረገውን ታሪክ የሚነግር ነው ።

፲፫ኛ ፡ ስለ ሚዶንና ስለ ሞዓባውያን የሚለው አስከንድርን ሲያመለክት ነው እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩ ፲፬ መጻሕፍቶች የዓለም ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንቀበላቸውም ሲሉ ይገኛሉ ። ምክን ያቱም መጻሕፍተ ብሉያት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከኢየሩሳሌም ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ግዕዝ እየተገለበጡ መምጣታቸውን በለማወቅ ይመስላል ። ባለ ማወቅ ነው ብለንም ነገሩን እንዳንተወው የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የኢትዮጵያን መሠረተ ታሪክ እና ውቃለን እያሉ በብዙ ሲደክሙ ይገኛሉ ፡ ታሪኩን ያውቁታል ብለን እንዳንቀበል ወደ መሠረቱ ገብተን መጻሕፍቱን ለመ መርመር የታሪክ ምንጭ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ስንመለከት ከኢትዮጵያ ክርስቲያን በተቀር ሌላ የዓለም ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችው ቅዱስ መጽሐፍ በጕድለት በሙል የተለያየ ሆኖ ስለሚታይ ፡ የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የጐደለው መጽሐፍ ጌቶች መሆናቸውን በለመገንዘብ ሙሉ ሁነው የሚገኙትን መጻሕፍቶች ከጐደሉዎቹ መጻሕፍቶች እናስተካክል የማለት አሳባቸውን ሲአቀርቡና እንዲአውም የኢትዮጵያን የመጻሕፍት ቅድምና ለመሠረዝ ሲሞክሩ ይታያሉ ። ከላይ የተጻፉ ፲፬ኙ መጻሕፍት እነሱ ከተቀበሉት ብሉይ ኪዳን ለመተካከል እኩል ለመሆን ትንሽ ጐደል የሚል መስሎ ቢታይም ሙሉ መስለው የሚታዩአቸው መጻሕፍቶችን ዝርዝር ከዚህ አስከትየ አመጣለሁ ።

፱፮ኛ ፡ ፩ኛ አሪት ዘፍጥረት ፡
፪ኛ ፡ አሪት ዘፀዓት ።
፫ኛ ፡ አሪት ዘሌዋውያን ።
፬ኛ ፡ አሪት ዘኍልቊ ።
፭ኛ ፡ አሪት ዘዳግም ።
፮ኛ ፡ መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ።
፯ኛ ፡ መጽሐፈ መሳፍንት ።
፰ኛ ፡ መጽሐፈ ሩት ።
፱ኛ ፡ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ።
፲ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ ።
፲፩ኛ ፡ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ።
፲፪ኛ ፡ መጽሐፈ ነገሥት ካልእ ።
፲፫ኛ ፡ መጽሐፈ ዜና መዋ. ቀዳማዊ ።
፲፬ኛ ፡ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልእ ።
፲፭ኛ ፡ መጽሐፈ እዝራ ።
፲፮ኛ ፡ መጽሐፈ ነህምያ ።
፲፯ኛ ፡ መጽሐፈ አስቴር ።
፲፰ኛ ፡ መጽሐፈ ኢዮብ ።
፲፱ኛ ፡ መዝሙራት ዘዳዊት ።
፳ኛ ፡ መጽሐፈ መኃልይ ።
፳፩ኛ ፡ መጽሐፈ ምሳሌ ።
፳፪ኛ ፡ መጽሐፈ መክብብ ።
፳፫ኛ ፡ ትንቢተ ኢሳይያስ ።
፳፬ኛ ፡ ትንቢተ ኤርምያስ ።
፳፭ኛ ፡ ሰቆቃወ ኤርምያስ ።
፳፮ኛ ፡ ትንቢተ ሕዝቅኤል ።
፳፯ኛ ፡ ትንቢተ ዳንኤል ።
፳፰ኛ ፡ ትንቢተ ሆሴዕ ።
፳፱ኛ ፡ ትንቢተ ኢዮኤል ።
፴ኛ ፡ ትንቢተ አሞጽ ።
፴፩ኛ ፡ ትንቢተ አብድዩ ፡
፴፪ኛ ፡ ትንቢተ ዮናስ ።
፴፫ኛ ፡ ትንቢተ ሚክያስ ።
፴፬ኛ ፡ ትንቢተ ናሆም ።
፴፭ኛ ፡ ትንቢተ እንባቆም ።
፴፮ኛ ፡ ትንቢተ ሰፎንያስ ።
፴፯ኛ ፡ ትንቢተ ሐጌ ።
፴፰ኛ ፡ ትንቢተ ዘካርያስ
፴፱ ኛ ፡ ትንቢተ ሚልክያስ ፡ ናቸው ።

እነዚህ ፴፱ቱ መጻሕፍት ሳይጐድሉና ሳይቈነጸሉ ተገኝተው እንኳ ቢሆን አንቀበላቸውም ብለው በተውዋቸው በ፲፱ቱ መጻሕፍቶች መቅረት ብቻ ጉዳቱ ምንም ከፍ ያለ ቢሆን ለጊዜው ብዙ አይደነቅም ነበር ፡ ነገር ግን ፴፱ኙ ቍጥር የሚገኙበት መጻሕፍቶች ምን ያህል ጉድለት እንዳለባቸው ለመግለጽ ከዚህ አስከትየ የምዘረዝረውን አንበቢ ያመልክት ።

ለአንባቢ እንዲመች ምክንያቱን መግለጽ የተገባ ስለሆነ ፡ እነዚህን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍቶች የዓለም ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ ከ፭ና ከ፮ ወይም ከ፯፻ ዓመተ ምሕረት በላይ ሲሆን ፡ እነዚህም መጻሕፍቶች የተገኙ ከኢየሩሳሌም ምሁራብ ስለሆነ ፡ አይሁድ የጌታችንን መወለድ ገና ነው በማለት ለነገሩ እንዲመቻቸው ዘመኑንና ትውልዱን እያሳጠሩ ኃይለ ቃሉንም እየለወጡ ጽፈውት ነው ። ስለዚህ ጥቃቅኑን ስሕተት ትተን ታላላቁን ስሕተት እንመልከት ።

ስለ ዘመኑ ቍጥር አቀናነስ በሚከተለው ክፍል እንመልከት ።

ክፍል ፲፩

፩ ኛ ፡ አሪት ዘፍጥረት ፩ ምዕራፍ ።

የአ.ትዮጵያ ቅዱስ መጽሐፍ	የውጭ አገር ቅዱስ መጽሐፍ
አዳም በ፪፻፴ ዘመኑ ሴትን ወለደ ።	ቁ. ፫ አዳምም ፪፴ ዘመን ተቀመጠ ልጅንም ወለደ ።
ቁ. ፭ ሴት በ፪፻፭ ዘመኑ ሄኖስን ወ ለደ ።	ቁ. ፭ ሴትም ፻፭ ዓመት ተቀመጠ ልጅም ወለደ ፡
ቁ. ፱ ፡ኄኖስ በ፻፺ ዘመኑ ቃይናን ወለደ ።	ቁ. ፱ ፡ኄኖስም ፺ ዓመት ተቀመጠ ቃይናንን ወለደ ፡
ቁ. ፲፪ ቃይናን በ፸ ዘመኑ መላልኤ ልን ወለደ ።	ቁ. ፲፪ ቃይናን በ፸ ዘመኑ መላልኤ ልን ወለደ ፡
ቁ. ፲፭ መላልኤልም ፷፭ ዓመት ተቀ መጠ ያሬድን ወለደ ፡	ቁ. ፲፭ መላልኤልም ፷፭ ዓመት ተቀ መጠ ያሬድን ወለደ ፡
ቁ. ፲፰ ያሬድም በ፻፷፪ ዓመት ፡ኄኖ ክን ወለደ ፡	ቁ. ፲፰ ያሬድ ም በ፻፷፪ ዓመት ፡ኄኖ ክን ወለደ ፡
ቁ. ፳፩ ፡ኄኖክም ፷፭ ዓመት ተቀመጠ ማቱሳላን ወለደ ፡	ቁ. ፳፩ ፡ኄኖክ ም ፷፭ ዓመት ተቀመጠ ማቱሳላን ወለደ ፡
ቁ. ፳፭ ማቱሳላ ፩፻፹፯ ዓመት ተቀመ ጠ ላሜህን ወለደ ፡	ቁ. ፳፭ ማቱሳላ ፩፻፹፯ ዓመት ተቀመ ጠ ላሜህን ወለደ ፡
ቁ. ፳፰ ላሜህም ፻፹፪ ዓመት ተቀ መጠ ኖኅን ወለደ ።	ቁ. ፳፰ ላሜህም ፻፹፪ ዓመት ተቀ መጠ ኖኅን ወለደ ።
ቁ. ፴፪ ኖኅም በ፭፻ ዓመት ሴምን ካምንና ያፌትን ወለደ ።	ቁ. ፴፪ ኖኅም በ፭፻ ዓመት ሴምን ካምንና ያፌትን ወለደ ።
ሴም በ፻፪ ዘመኑ አርፋክስድን ወለደ ።	ሴም በ፻፪ ዘመኑ አርፋክስድን ወለደ ።
አርፋክስድ በ፴፭ ዓመቱ ሄበርን ወለደ ።	አርፋክስድ በ፴፭ ዓመቱ ሄበርን ወለደ ።
ሄበር በ፴፬ ዘመኑ ፋሌቅን ወለደ ።	ሄበር በ፴፬ ዘመኑ ፋሌቅን ወለደ ።
ፋሌቅ በ፴ ዘመኑ ራግውን ወለደ ።	ፋሌቅ በ፴ ዘመኑ ራግውን ወለደ ።
ራግው በ፴፪ ዘመኑ ሴሩህን ወለደ ።	ራግው በ፴፪ ዘመኑ ሴሩህን ወለደ ።
ሴሩህ በ፴ ዘመኑ ናኮርን ወለደ ።	ሴሩህ በ፴ ዘመኑ ናኮርን ወለደ ።
ናኮር በ፳፱ ዘመኑ ታራን ወለደ ።	ናኮር በ፳፱ ዘመኑ ታራን ወለደ ።
ታራ በ፸ ዘመኑ አብርሃምን ወለደ ።	ታራ በ፸ ዘመኑ አብርሃምን ወለደ ።

፩ኛ ፡ በኦሪት ዘፍጥረት ላይ ከመገሥፀሪያ ሙሴ እንደጻፈው ምን ማስረጃ ይገኛል ? ። ፫ኛ ፡ ኡ. ዘፍ. ፯ ፲፩ "አመ ክነ ፮፻ ወ፩ዶ ዓመተ ሕይወቱ ለኖኅ በካልእ ወርኅ በ፲ሩ ወሠኑዩ ለጽልመት ,, ፭ኛ ፡ ፷ ፬ "ወነበረት ይእቲ ታቦት በሳብዕ ወርኅ አመ አሥሩ ወሰኑዩ ለጽልመት ,, ይላል ፡ ቁ. ፲፫ "ወአመ ክነ ፮፻፩ተ ወ፩ዶ ዓመተ እምነ ሕይወቱ ለኖኅ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ ቀዳማይ ለጽልመት ,, ይላል ። ፯ኛ ሕዝቅኤል ፷ ፩ "ወክነ አመ ሣድስ ወርኅ በኃምስ ሠርቅ ,, ይላል ጨረቃን ማለቱ ነው ። ፰ኛ ወነበበኒ እግዚአ ብሔር በታስዕ ዓመት በዐሥር ወርኅ በዐሡረ ሠርቅ ይላል ጨረቃ በታየች ባሥር ቀን ማለት ነው ። ፱ኛ ፡ ትንቢተ ሐጌ ፪ ፪ "በሳብዕ ወርኅ በሠዱሱ ለጽልመት ,, ይላል ጨረቃ በጨለመች በ፯ ቀን ማለቱ ነው ። ቁ. ፱ "ሐልዩ በልብክሙ ዘእምአሚ ቀዳሚት ዕለት ወዘእምድኅሬሃ ዘአመ ተሰዐወ ለጽልመት በታስዕ ወርኅ ,, ያለው የጨረቃ ብርሃን እየቀነሰ ጽልመት እየበዛ እስከ ፱ኛ ስለ ደረሰ ዘአመ ተሰዐወ ለጽልመት አለ ። ከላይ ስለ ጨረቃ ብርሃንና ጨለማ የወር መቈጠሪያነት የተጻፉ ማስረጃዎች ከኦሪ. ዘፍ. ፩ ፲፩ ፡ ፷ ፬ ፡ ሕዝ. ፷ ፩ ፡ ፸፬ ፩ ፡ ትንቢተ ሐጌ ፪ ፪-፲፱ ለጊዜው ፷ ቱን መረጃዎች ማስተዋል ነው ። በዚህ መሠረት በፀሐይ ስለሚቈጠሩ በ፪ቱ ወሮች ውሥጥ ስለአሉ ቀኖች ጽልመትና ብርሃን በጨረቃ ላይ ባ፲፭ት ባ፲፭ት ቀን የሚፈራረቁበትን ዋና ምሥጢር የዓለም ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንቶች እስከ ዛሬ መሠረቱን ለማግኘት የቻሉ አለመሆናቸውን እነሱ ያመጡት መጽሐፍ ይመሰክራል ።

አንባቢ ሆይ! ከላይ በተጠቀሱት ጽሑፎች ላይ አስተውለህ የተመለከትህ እንደሆን የጽልመትንና የጨረቃን ነገር ሲያስታውስ አታገኘውም ፡ የሮማ ሊቃውንት የመን ግሥተ ሰማያት መክፈቻ በመንበረ ጴጥሮስ ለተቀመጠው ተሠጥቷል እያሉ የኢትዮጵያን ታሪክ ከመሰርሰር የመጻሕፍቱን መሠረት መርምሮ እርግጠኛውን ነገር መከተል ይሻላቸው ነበር ። እስከ ዛሬ ድረስ የጽልመትንና የብርሃንን መፈራረቅ የጨረቃን ወር ባ፲፭ት ባ፲፭ት ቀን መሆኑን ከላይ እንደተጻፈው መላእክት የተፈጠሩበትን መርምረው መረጃውን ሰያገኙ እንዲሁ በልማድ እንደሚኖሩ ፡ ኦሪት ዘፍጥረትንም ማን እንደጻፈው መረጃ ሳይዙ እንደዚሁ በልማድ ሲጓዙበት እንደሚኖሩ ፡ የጨረቃን ወር መግኛም ጽልመትና ብርሃንን እንዲሁ በልማድ ሲጓዙ ይገኛሉ እንጂ እርግጠኛውን መሠረት እንዳላገኙት ከላይ እንዳመለከትኩት የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል ። አሁን ፭ድ ጥያቄ የዓለምን ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንቶች ብጠይቃቸው እርግጠኛውን መልስ ለመስጠት አይደፍሩም ። ምክንያቱም መጽሐፈ ኄኖክን አንቀበልም በማለታቸው ነው ፡ ጥያቄ የተባለውም በቀን ፭፬ት ሰዓቶች አሉ የምንላቸው ከወዴት እንደመጡ ፲፪ ሰዓተ መዓልት ፲፪ ሰዓተ ሌሊት የተባሉ መሠረታቸው ከምን እንደሚገኝ የሚነግረኝ ማለቱ ነው ።

፱፱ኛ ፡ የዚህን መሠረት ለማግኘት ከመጻሕፍቱ አስማምቶ የሚአስረዳ ከዓለም ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይገኛል ለማለት አያስደፍርም ፡ ማለት ከኄኖክ መጽሐፍ የዓለም ቤተ ክርስቲያን ሊቃወንት የመጻሕፍቱን መሠረት ለመመርመር በጥብቅ አስበውበት ቢሆን ወደ መሠረቱ እየገቡ ቢመረምሩ ስለ መላእክት ተፈጥሮ በሰፊው ሙሴ በጻ

ፈው በዙፋሌ ለማግኘት በቻሉ ነበር ፡ አሁንም ለወደፊቱ መጽሐፈ ዙፋሌን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተቀብለው በሰፈው ከተረዱ በኋላ ሊጠቀሙበት ይችላሉ ። መጽሐፈ ዙፋሌን ቢቀበሉ አሪት ዘፍጥረትን በሰፈው ለመረዳት ይመቻቸው ነበር ። መጽሐፈ ዙፋሌን ሙሴ እንደጻፈው የሚአስረዳውን ትተው ከመገሥመሪያው ላይ ሙሴ እንደጻፈው የማያስረዳውን እንቀበላለን ማለት አጥጋቢ አይደለም ። ስለ ጨረቃ ከኄኖክ፡ ስለ ጨረቃ መንገድ ብርሃንና ጽልመት እየተፈራረቁ እንደምን እንደሚሄዱ ጨረቃ የፀሐይን መንገድ በኬክሮስ እንደምን እንድትሰፍረው ፡ ፩ዲቱ ዕለት ፩ድ ዓመት ፡ ፩ዲቱ ዓመት ፩ድ ቀን ስትሆን ሌሊቱና መዓልቱ የሚታጠፍበትን ለማወቅ ፡ ሌሊት ስለ ተባለ ሁሉ ሌሊት ፡ መዓልት ስለ ተባለ ሁሉ መዓልት አይደለምና ይህን ጥበብ ማወቅ ለወጣቶች ዋና ጥቅም ስለሆነ ያ፩ዱን ዓመት የጨረቃ መንገድ ልገልጠው ስለ ወደድሁ ፡ ከኄኖክ ምንጭ ፤ ዓለም የተፈጠረ በዕለተ እኁድ ወሩም ማያዝያ ነው ። ረቡዕ ጨረቃ ከዋክብት በቀዳሚ ሌሊት ተፈጥረዋል ። በቀዳማዊ ሰዓተ መዓልት ፀሐይ ተፈጥራለች ፡ ጨረቃ ረቡዕ በቀዳማዊ ሰዓተ ሌሊት ስትፈጠር ጽልመት አልነበረም ሙሉ ብርሃን ነው ። ምንም የጨረቃን መንገድ ለመመርመር ቢሆን ዕለታቱን ከመሠረታቸው እጀምራለሁ ።

የጽልመትና የብርሃን አቈጣጠር

ወር	ሚያዝያ		ወር	ግንቦት		ወር	ሰኔ	
	ጽልመት	ብርሃን		ጽልመት	ብርሃን	ጽልመት		ብርሃን
፩	እኁድ		፩	፭፩ ሠሉስ	፲፬	፩ ፭፩	ሐሙስ	፲፬
፪	ሰኑይ		፪	፲፬ ረቡዕ	፲፭	፪ ፲፬	ዓርብ	፲፭
፫	ሠሉስ		፫	፲፭ ሐሙስ	፲፮	፫ ፲፭	ቀዳም	፲፮
፬	ረቡዕ	፲፫	፬	ዓርብ ፮	፲፫	፬	እኁድ ፲፯	፲፫
፭	፲ ሐሙስ	፲፮	፭	፲ ቀዳም	፲፮	፭ ፲	ሰኑይ	፲፮
፮	፲፬ ዓርብ	፲፭	፮	፲፬ እኁድ	፲፭	፮ ፲፬	ሠሉስ	፲፭
፯	፭፩ ቀዳም	፲፬	፯	፭፩ ሰኑይ	፲፬	፯ ፭፩	ረቡዕ	፲፬
፰	፭፰ እኁድ	፲፫	፰	፭፰ ሠሉስ	፲፫	፰ ፭፰	ሐሙስ	፲፫
፱	፴ ሰኑይ ፱	፲፪	፱	፴ ረቡዕ ፯	፲፪	፱ ፴	ዓርብ ፲፱	፲፪
፲	፴፭ ሠሉስ	፲፩	፲	፴፭ ሐሙስ	፲፩	፲ ፴፭	ቀዳም	፲፩
፲፩	፴፱ ረቡዕ	፲	፲፩	፴፱ ዓርብ	፲	፲፩ ፴፱	እኁድ	፲
፲፪	፵፫ ሐሙስ	፱	፲፪	፵፫ ቀዳም	፱	፲፪ ፵፫	ሰኑይ	፱
፲፫	፵፯ ዓርብ	፰	፲፫	፵፯ እኁድ	፰	፲፫ ፵፯	ሠሉስ	፰
፲፬	፶፩ ቀዳም ፯	፯	፲፬	፶፩ ሰኑይ ፯	፯	፲፬ ፶፩	ረቡዕ ፳፫	፯
፲፭	፶፭ እኁድ	፮	፲፭	፶፭ ሠሉስ	፮	፲፭ ፶፭	ሐሙስ	፮
፲፮	፶፱ ሰኑይ	፭	፲፮	፶፱ ረቡዕ	፭	፲፮ ፶፱	ዓርብ	፭
፲፯	፷፫ ሠሉስ	፬	፲፯	፷፫ ሐሙስ	፬	፲፯ ፷፫	ቀዳም	፬

፲	፲፭	ረቡዕ	፭
፲፩	፲፮	ሐሙስ	፮
፲፪	፲፯	ዓርብ	፯
፲፫	፲፰	ቀዳም	፩
፲፬	፲፱	እኁድ	፪
፲፭	፳	ሰኑይ	፫
፲፮	፳፩	ሠሉስ	፬
፲፯	፳፪	ረቡዕ	፭
፲፰	፳፫	ሐሙስ	፮
፲፱	፳፬	ዓርብ	፯
፳	፳፭	ቀዳም	፩
፳፩	፳፮	እኁድ	፪
፳፪	፳፯	ሰኑይ	፫
፳፫	፳፰	ሠሉስ	፬
፳፬	፳፱	ረቡዕ	፭
፳፭	፴	ሐሙስ	፮
፳፮	፴፩	ዓርብ	፯
፳፯	፩	ቀዳም	፩
፳፰	፪	እኁድ	፪
፳፱	፫	ሰኑይ	፫
፴	፬	ሠሉስ	፬
፴፩	፭	ረቡዕ	፭

ወር ጥቅምት

፲	፲፭	እኁድ	፪
፲፩	፲፮	ሰኑይ	፫
፲፪	፲፯	ሠሉስ	፬
፲፫	፲፰	ረቡዕ	፭
፲፬	፲፱	ሐሙስ	፮
፲፭	፳	ዓርብ	፯
፲፮	፳፩	ቀዳም	፩
፲፯	፳፪	እኁድ	፪
፲፰	፳፫	ሰኑይ	፫
፲፱	፳፬	ሠሉስ	፬
፳	፳፭	ረቡዕ	፭
፳፩	፳፮	ሐሙስ	፮
፳፪	፳፯	ዓርብ	፯
፳፫	፳፰	ቀዳም	፩
፳፬	፳፱	እኁድ	፪
፳፭	፴	ሰኑይ	፫
፳፮	፴፩	ሠሉስ	፬
፳፯	፩	ረቡዕ	፭
፳፰	፪	ሐሙስ	፮
፳፱	፫	ዓርብ	፯
፴	፬	ቀዳም	፩
፴፩	፭	እኁድ	፪

ወር ኅዳር

፲	፲፭	ሠሉስ	፫
፲፩	፲፮	ረቡዕ	፬
፲፪	፲፯	ሐሙስ	፭
፲፫	፲፰	ዓርብ	፮
፲፬	፲፱	ቀዳም	፯
፲፭	፳	እኁድ	፩
፲፮	፳፩	ሰኑይ	፪
፲፯	፳፪	ሠሉስ	፫
፲፰	፳፫	ረቡዕ	፬
፲፱	፳፬	ሐሙስ	፭
፳	፳፭	ዓርብ	፮
